# የእንስሳት ልማት ኢንስቲትዩት

# የ10 ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ

(2013-2022)

ሰኔ 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ማውጫ


የዋና ዳይሬክተሩ መልእክት ........ III

መግቢያ ........ V

ክፍል አንድ:- ዘርፉ ያለበት ሁኔታዎች ትንተና ........ 1

1.1. ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያዎች ........ 1

1.2. የግብርናው ዘርፍ ያለበት ሁኔታ ........ 1

1.3. የእንስሳት ዘርፍ ሁኔታ ........ 2

1.4. የእንስሳት ልማት ኢንስቲትዩት ሁኔታ ........ 3

1.5. የእቅዱ መነሻዎች ........ 3

1.5.1. ኢትዮጵያ አፍሪካዊት የብልፅግና ተምሳሌት (2013-2022) የፌደራል መንግስት የ 10 ዓመት የልማት ዕቅድ እንደመነሻ፣ 3

1.5.2 የግብርና ሚኒስቴር 10 ዓመት መሪ እቅድ እንደ መነሻ ........ 4

1.5.3. የግብርና ሚኒስቴር 10 በ10 ዕቅድ እንደ መነሻ ........ 4

1.5.4. ብሔራዊ የርቢ ፖሊሲና ስትራቴጂ እንደ መነሻ ........ 4

1.6. የባለፉት አሥር ዓመታት ዋና ዋና አፈጻጸሞች ........ 4

1.6.1. የዝርያ ማሻሻያ ግብዓት አቅርቦትና ሥርጭት ........ 4

1.6.2. ፈሳሽ ናይትሮጂን ምርትና ሥርጭት ........ 5

1.6.3. የእንስሳት ምርትና መኖ ማቀነባበር አፈጻጸም ግምገማ ........ 8

1.6.4. የወጪ ንግድ እና ተኪ ምርቶች አፈጻጸም ........ 8

1.6.5. የሥጋና የእርድ ተረፈ-ምርት አፈፃፀም ........ 8

1.6.6. የማርና ሰም የወጪ ንግድ አፈፃፀም ........ 9

1.6.7. የዓሣ ሥጋ የወጪ ንግድ አፈፃፀም ........ 10

1.6.8. የዶሮ ስጋ ምርት አፈፃፀም ........ 10

1.6.9. የእንስሳት መኖ ምርት አፈፃፀም ........ 11

1.6.10. የወተትና የወተት ምርት ማቀነባበር አፈጻጸም ........ 12

1.7. ዋና ዋና የድጋፍ ስራዎች አፈጻጸም ........ 13


1.7.1. የግብይት ሥራዎች ........ 13

1.7.2. የአቅም ግንባታ ሰልጠና እና የቴክኒክ ድጋፍ ስራዎች ........ 14

1.7.3. የጥናትና ምርምር ሥራዎች ........ 14

1.7.4. የኢንቨስትመንት የድጋፍ ስራዎች ........ 14
1.7.5. የግንባታ እና ኢንጂነሪንግ ድጋፍ :የተቀናጀ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ........ 15
1.7.6. ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ........ 15
1.8 የውስጣዊና ውጫዊ ሁኔታ ዳሰሳ ........ 16
1.8.1 የውስጣዊ ሁኔታ ዳሰሳ ........ 16
1.8.2 የውጫዊ ሁኔታ ዳሰሳ (መልካም አጋጣሚዎችና ስጋቶች - PESTEL) ........ 17
1.8.3 አስቻይና ፈታኝ ሁኔታዎች ........ 18
1.8.4 የባለድርሻ አካላት ትንተና ........ 19
1.9. ተልዕኮ፣ራዕይ፤ዓላማና ዕሴቶች ........ 22
1.9.1. ዓላማ ........ 22
1.9.2. ተልዕኮ ........ 22
1.9.3. ራዕይ ........ 22
1.9.4. እሴቶች ........ 22
ክፍል ሁለት:- እስትራቴጂያዊ ዓላማዎች፤ ግቦች፣ዒላማዎች እና የማስፈፀሚያ ስልቶች ........ 23
2.1 እስትራቴጂያዊ ዓላማዎች ........ 23
2.2 እስትራቴጂያዊ ግቦች ........ 23
2.3. የግብ ዒላማዎች በዋና ዋና አመልካቾች ........ 23
2.4 ዋና ዋና የስትራቴጂክ እቅዱ ማስፈጸሚያ ስልቶች ........ 28
2.4.1 ቅንጅታዊ ስራዎችን ማጠናከር ........ 28
2.4.2 የግል ባለሀብቱን ሚና እና ተሳትፎ ማረጋገጥ ........ 28
2.4.3 አስፈላጊ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣አዋጆች ደንቦችና መመሪዎችን ተግባራዊ ማድረግ ........ 28
2.4.4 የፋይናንስ ምንጭን ማስፋትና በግባቡ መጠቀም ........ 28
ክፍል ሦስት:-የስጋት ግምገማ እና ስጋቶችን ለመቀነስ የሚተገበሩ ስትራቴጂዎች ........ 29
3.1. የ ስጋት ግምገማ ........ 29
3.2. ስጋቶችን ለመቀነስ የሚያስችሉ ስትራቴጂዎች ........ 30
ክፍል አራት : የክትትልና ግምገማ ስርዓት ........ 32
ክፍል አምስት:- አባሪዎች ........ 33
5.1. ከ2013-2022 በጀት ዓመት የሚተገበሩ ፕሮጀክቶች ........ 39
5.2. የሰው ሃይል ፍላጎት ........ 39

# የዋና ዳይሬክተሩ መልዕክት



የኢትዮጵያ ግብርና በአጠቃላይ ከጥቂት ዓመታት ወዲህ እጅግ አበረታች ለውጦችን በማስመዝግብ ላይ ይገኛል። እንደምሳሌ ሊነሳ የሚችል አንዱና ዋነኛው ጉዳይ ላለፉት የለውጥ ዓመታት በግብርናው ዘርፍ የታዩ ለውጦች በእርግጥም ግብርናችን ከተሰራበት መሠረታዊ ለውጥ አስመዝግቦ ለኢትዮጵያዊያን ብቻ ሳይሆን መላውን አፍሪካ መመገብ የሚያስችል አቅም ያለው መሆኑን በተለይም ደግሞ ላለፉት ጥቂት የምርት ዘመናት የታየው ለውጥና የመጣው ውጤት ተስፋ ሰጪ መሆኑን አፋችንን ሞልተን መናገር እንችላለን። በኢትዮጵያ ግብርናው ለብዙዎች ተስፋ ሰጭ ሆኖ ለመታየቱ ቋሚ ምስክር ነው። በአገር በቀል ኢኮኖሚ ሪፎርም በመንግስት ትኩረት የተሰጣቸው መስኮች ውስጥ ግብርና አንዱና ዋነኛው ነው። በግብርና ስር ደግሞ የተፈጥሮ ሀብት፣ የእንስሳት ልማትና የሰብል ልማቱ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶባቸው እየተሰሩ ያሉ የግብርናው ወሳኙ አንጓ ናቸው።

ኢትዮጵያ ለዘመናት ሲነገር እንደነበረው ባላት የእንስሳት ሀብት ከአፍሪካ ቀዳሚው ደረጃ ላይ እየተጠቀሰች ነው። ነገር ግን ከብዛት ባሻገር ከእነዚህ እንስሳት የተገኘው ውጤት በአጥጋቢ ሁኔታ አለ ብሎ ደፍሮ ለመናገር ያስቸግራል። የእንስሳት ዝርያ ማሻሻል ላይ የተሰሩ ስራዎች አጥጋቢ አለመሆናቸው፣ የእንስሳቱ የጤና አጠባበቅ ሁኔታ በሚገባ አለመሻሻሉ፣ የእንስሳት መኖን ምርትና ምርታማነት ማሻሻል ላይ የተሰራው ስራ አጥጋቢ አለመሆኑ በተለይም የእንስሳቱ ምርትና ምርታማነት ማሻሻል እንደ ማነቆ ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው። በመሆኑም እነዚህ ማነቆዎች ከመሠረቱ እንዲለወጡ ለእንስሳት ልማት ዘርፍ መንግስት ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ይገኛል። እንስሳት ልማት ኢንስቲትዩት ይህንን በትኩረት እንዲመራ መዋቅር ሆኖ እንዲደራጅ በማድረግ በዋናነት ልማቱን ለመደገፍ በጥናትና ምርምር፣ በአቅም ግንባታና ማማከር ላይ ትኩረት በማድረግ በትኩረት እየተመሩ ይገኛሉ።

መንግስት ለዚህ ዘርፍ ልዩ ትኩረት የሰጠ መሆኑን ከሚያሳዩ ብዙ ነገሮች አንዱ በክቡር ጠቅላይ ሚኒስትራችን ሀሳብ አመንጪነት የተቀረፀው የሌማት ትሩፋት ፕሮግራም ሲሆን ላለፉት ሶስት ዓመታት ተተግብሮ እጅግ የሚያበረታታ ውጤት ተገኝቶበታል። ይህ ፕሮግራም ለሚቀጥሉት ጥቂት ዓመታት በዚሁ ከቀጠለ ዘርፉ ለምግብና ሥነ-ምግብ ዋስትና ለሥራ ዕድል ፈጠራ በአጠቃላይም ለሀገራችን ብልጽግና የራሱን ጉልህ አስተዋጽኦ ሊያበረክት እንደሚችል ትልቁ ማሳያ ይሆናል።

እነዚህ ከላይ የተቀመጡ ፕሮግራሞች በአግባቡ ተመርተው ውጤት ማምጣት መቻላቸው በዘፈቀደ ስለተመሩ ሳይሆን በእቅድ ተመርተው እቅዱ ደግሞ በጥብቅ ዲሲፒሊን ስለተፈፀመ ነው። የእንስሳት ልማት ኢንስቲትዩትም ይህንን በአግባቡ ስለሚረዳ ለሚቀጥሉት አስር ዓመታት የሚተገበር በተለይም በእንስሳት ዝርያ ማሻሻል፣ በጤና አጠባበቅ፣ በመኖ ምርትና ምርታማነት ማሻሻል ዙሪያ ዝርዝር እቅድ አዘጋጅቶ የትግበራ መርኃ ግበሩ ተቀምጦላት በንኡስ ዘርፉ ካሉት ባለድርሻ አካላት ጋር መክረውበት፣ በኢንስቲትዩቱ እና ጉዳዩ በሚመለከታቸው የግብርና ሚኒስቴር የሥራ ኃላፊዎች ሀሳብ ተሰጥቶበት እንዲፀድቅ ተደርጓል።

ስለሆነም ይህ እቅድ በኢንስቲትዩቱ ይዘጋጅ እንጂ ትግበራው ላይ የሁሉንም ባለድርሻ አካላት በተለይም በንኡስ ዘርፉ የተሰማሩ ተመራማሪዎች፣ ባለሀብቶች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ዓለም አቀፍ፣ አህጉር አቀፍና ሀገር በቀል አጋር ድርጅቶች፣ በየደረጃው ያሉ የመንግስት አደረጃጀቶች፣ የንኡስ ዘርፉ ማህበራት በተለይም ደግሞ የሙያ ማህበራት...ወዘተ አስተዋፅዖዋቸው የጎላ በመሆኑ ይህንን እቅድ የራሳቸው አድርገው በመውሰድ ለትግበራው ሁሉ የሚጠበቅባቸውን እንዲያበረክቱና ሙያዊ አስተዋፅኦ እንዲያድርጉ ጥሪዬን አስተላልፋለሁ። ኢትዮጵያ ለጀመረችው የብልፅግና ጉዞ በእንስሳት ልማት ዘርፉ የድርሻችንን እንድናበረክትና የሌማት ትሩፋቱ አሁን ካስገኛው ውጤት በላይ የላቀ ውጤት እንድናስመዘግብ እጅ ለእጅ ተያይዘን የየድርሻችንን አበርክቶ አጠናክረን እንቀጥል በማለት ጥሪዬን በኢንስቲትዩቱና በራሴ ስም እያስተላለፍኩ ስትራቴጂውን በማዘጋጀት ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው የመራው አቶ ታሪኩ ተካ እንዲሁም ስራውን በአግባቡ ለሰሩት አቶ  አለሐኝ አገኝ፣ ለአቶ ተሾመ ቢራቱ፣ ለአቶ መስፍን ክፈሌ፣ ለአቶ አዲስ ፍቅሬ፣ ዶ/ር ኢሳያስ ተሰማ፣ ዶ/ር ቡላ አገኘሁ እና አቶ ሌሊሳ ጉዲሳ ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

አሥራት ጤራ (ፒኤችዲ)
ዋና ዳይሬክተር

# መግቢያ

ሀገራችን ኢትዮጵያ ለእንስሳት ሀብት ልማት ተስማሚ የአየር ንብረት እና ሰፊ ብዝሃ-ህይወት ያላት አገር ናት። ኢትዮጵያ በእንስሳት ሀብቷ ከአፍሪካ ቀዳሚ ስትሆን በማዕከላዊ ስታትስቲክስ አገልግሎት የ2012 ዓ.ም ሪፖርት መሰረት 61.59 ሚሊዮን ዳልጋ ከብት፣ 32.85 ሚሊዮን በጎች፣ 36.80 ሚሊዮን ፍየሎች 48.13 ሚሊዮን ዶሮዎች፣ 3.73 ሚሊዮን ግመሎች፣ 9.23 ሚሊዮን አህዮች እና 6,792,719 የንብ ቀፎ ያላት ሀገር ስትሆን ይህም በእንስሳት ሀብት ከአፍሪካ ቀዳሚ ያደርጋታል። ይሁን እንጂ ካለው የእንስሳት ሀብት አንጻር የአርብቶ/አርሶ አደሩ ተጠቃሚነትም ሆነ ሀገሪቱ ከዘርፉ የምታገኘው ኢኮኖሚ ጥቅም ዝቅተኛ እንደሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ለዚህም ከሚጠቀሱት ዋንኛ ምክንያቶች መካከል የሀገር በቀል ዝርያዎች የሚሰጡት ምርት ዝቅተኛ መሆንና በቂ የተሻሻሉ ዝርያዎች ያለመኖር፣ በብዛትም ሆነ በጥራት የእንስሳት መኖ ዕጥረት፣ የእንስሳት ጤና አገልግሎት ሽፋን ዝቅተኛ መሆን፣ ዘመናዊና ገበያ ተኮር የእንስሳት እርባታ ያለመስፋፋት፣ የእንስሳት ምርትና ተዋጽኦ የማቀነባበርና እሴት የመጨመር ክህሎትና እውቀት ዝቅተኛ መሆን ይጠቀሳሉ። ለአብነት ያህልም በሀገራችን ካሉት ጠቅላላ የዳልጋ ከብት፣ የበግና ፍየል የእንስሳት ሀብት ዝርያቸው የተሻሻሉት እንስሳት በቅደም ተከተል ከ2.67%፣ ከ0.32%፣ እና 0.03% ያልዘለለ መሆኑን የማዕከላዊ ስታትስቲክስ አገልግሎት መረጃ ያመለክታል። ከተቀነባበሩ የእንስሳት ምርትና ተዋጽኦ የተገኘው አመታዊ የወጪ ምርት ገቢም ከ 121.17 ሚሊዮን ዶላር ያለፈ አይደለም።

ሀገራችን ካሏት እምቅ የእንስሳት ሀብት አኳያ ማግኘት የነበረባትን ጥቅም ማግኘት እንድትችል ከዚህ በፊት የእንስሳት ዝርያዎችን በማሻሻል የእንስሳት ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ብሔራዊ የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ኢንስቲትዩት እንዲሁም ከእንስሳት የተገኙ ምርቶችን ወይም የእንስሳት ምርትና ተዋፅዖን በአግባቡ በማቀነባበር ለውጪ ምንዛሪ ግኝት እንዲውሉ፣ ከውጪ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ለመተካት እና ለዜጎች ምግብነት እንዲውሉ፣ የግል ባለሀብቱ በዘርፉ መዋዕለ ንዋዩን/Investment/ እንዲያፈስ በአቅም ግንባታ፣ በምርምር እና ማማከር የቴክኒክ ድጋፍ እንዲያደርግ የኢትዮጵያ ሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት በደንብ ተቋቁመው የተሰጣቸውን ተግባርና ኃላፊነት ሲያከናውኑ ቆይተዋል። እነዚህን ሥራዎች ሲያከናውኑ የቆዩት ብሔራዊ የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ኢንስቲትዩት እና የኢትዮጵያ ሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ይበልጥ ውጤታማ እንዲሆኑ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣን እና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀጽ 97 ተራ ቁጥር 12 እና 15 የተመለከቱትን ሁለቱን ኢንስትዩቶች ማዋሄድ በአንቀጽ 47 መሠረት የእንስሳት ልማት ኢንስቲትዩትን አቋቁሟል። በአዋጁ አንቀጽ 99 ተራ ቁጥር 25 መሠረት ቀደም ሲል ለሁለቱ ኢንስቲትቶች ተሰጥቶ የነበረው መብት እና ግዴታ አዲስ ለተቋቋመው የእንስሳት ልማት ኢንስቲትዩት ተሰጥቷል። በዚሁ መሠረት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 506/ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባር ለመወጣት የሚያስችል አደረጃት/Organogram/ አዘጋጅቶ የሠራተኞች ድልድል በማካሄድ ወደ ስራ ገብቷል። ስለሆነም በደንቡ የተሰጠውን ተግባርና ሃላፊነት በመወጣት በእንስሳት ልማቱ ዘርፍ ፈጣንና ዘላቂ እድገት ለማስመዝገብ ከሀገሪቱ የልማት እቅድና ከግብርና ልማት መሪ እቅድ ጋር የሚጣጣምና የሚናበብ ስትራቴጂክ እቅድ ማዘጋጀት በማስፈለጉ ይህ የስትራቴጀክ እቅድ ሰነድ ተዘጋጅቷል።

በእቅዱም በክፍል አንድ ዘርፉ ያለበት ሁኔታ ትንተና፣ በክፍል ሁለት ስትራቴጂያዊ አላማዎች፣ ግቦች፣ ኢላማዎችና መስፈጸሚያ ስልቶች፣ በክፍል ሦስት ስጋቶችና ማስወገጃ ስልቶች፣ በክፍል አራት የክትትል ግምገማ ስርአት፣ በመጨረሻም የሚደረስባቸው ኢላማዎች፣ የሰው ሃይል ፍላጎትና ፕሮጀክቶች በአባሪነት ተካተው ቀርበዋል።

# ክፍል አንድ:- ዘርፉ ያለበት ሁኔታዎች ትንተና

## 1.1.ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያዎች

ለግብርና ዘርፍ ተዋናዮች የሚሰጠው ድጋፍ በጥናት ላይ ተመስርቶ እንዲሻሻል ሥራዎች በመከናወን ላይ ይገኛሉ። ከዚህ አንጻር ለአርሶ አደሩ የሚቀርቡ ግብዓቶች ግብይት የሚቀላጠፍበትና ከመንግስትም የተለየ ድጋፍ የሚያገኝበት ሁኔታ የተመቻቸ ሲሆን ለመስኖ ልማትና እርጥበት መቋጠር የተለየ ትኩረት እንዲሰጥ ተደርጓል። ለግብርና ልማት ሁሉን አቀፍ ድጋፍ በመስጠት የግብርና ምርታችን በአስተማማኝ ሁኔታ በተከታታይ የሚያድግበት መንገድ እየተመቻቸ ሲሆን የኢንዱስትሪ፣ የማዕድንና የቱሪዝም ዘርፎችም በተመሳሳይ ከፍተኛ ትኩረት እያገኙ ነው። አነስተኛና ሰፋፊ የመስኖ ልማትን ማስፋፋት፣ ለግብርና ግብዓትና ፋይናንስ ማቅረብ፣ የእንስሳት እርባታ ምርታማነትን መጨመር፣ የተፈጥሮ ሀብት አጠባበቅ የሁሉንም ትኩረትና ተሳትፎ አግኝቶ ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ፣ የግብርና አመራረት ዘዴን ማሻሻል፣ ድህረ ምርት ብክነትን መቀነስ፣ በጥናት ላይ የተመሠረተ የምግብ ዋስትና ሥርዓት ተግባራዊ ማድረግ፣ ዋና ዋና ሰብሎችን በተለይም በአጭር ጊዜ ስንዴን፣ የቢራ ገብስን፣ የምግብ ዘይትና ጥሬ ዕቃዎችን ሙሉ በሙሉ በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ የማድረግ ስራዎች ሲሰሩ ቆይተዋል። የተወሰኑ ገቢ ምርቶችን የመተካት ስትራቴጂ ተግባራዊ ከመሆኑም በላይ በዓለም አቀፍ ትስስር የሚመራው የኢኮኖሚ ስትራቴጂያችን በዋናነት ኤክስፖርት መር መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ እየወጣባቸው ያሉ ነገር ግን በትንሽ ጥረት ንጽጽራዊ አቅም ሊፈጠርባቸው የሚችሉ እንደ ምግብ ዘይት፣ ስንዴና የግብርና አግሮ ፕሮሰሲንግ ገቢ ምርቶችን በሀገር ውስጥ በማምረት የመተካት ስትራቴጂን በመከተል ሰፊ ሥራዎች በመሠራት ላይ ይገኛሉ።

የሥራ ፈጠራንና የቢዝነስ ምህዳሩን በማሻሻል ረገድ የሀገር ውስጥ የሥራ ፈጠራንም ሆነ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት መሠረተ-ልማትን ያካተቱና እስካሁን የተሰሩ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ጥቅም ላይ እንዲውሉ የማድረግ፣ የቢዝነስ ከባቢያዊ ሁኔታን የማሻሻል፣ አላስፈላጊ ቢሮክራሲን የማስወገድ እና የብድር አቅርቦት የማሻሻል ሪፎርም ተጠናክሮ እንዲቀጥል ተደርጓል። የግሉ ዘርፍ በኢኮኖሚው ውስጥ ያለውን ሚና ከማሳደግ አኳያም በኢኮኖሚው ውስጥ የነበረውን ሚናና ያጋጠሙትን ፈተናዎች በዝርዝር በጥናት በመፈተሽ ዘርፉ የሚጠበቅበትን ሚና በአግባቡና በተሻለ ሁኔታ እንዲወጣ ምቹ ሁኔታዎችን የሚፈጥሩ የኢኮኖሚ ሪፎርም እርምጃዎች በቀጣይነት ተግባራዊ በመደረግ ላይ ይገኛሉ። በዚህ ረገድ የሀገር ውስጥና የውጪ ባለሀብቶችን ተሳትፎ ለማሳደግ የሀገሪቱን የቢዝነስ ከባቢያዊ ሁኔታ በማሻሻል ረገድ የሚሠራው ሥራ በትንሹ በመፍጨርጨር የሚታትረውን ቢሮክራሲያችንን ጠልፎ የሚጥል ሣይሆን የሚደግፍና የሚያሳድግ እንዲሆን በርካታ ሥራዎች በመከናወን ላይ ናቸው። ይህ ማሻሻያ በፋይናንስ ዘርፉ ከሚደረገው ማሻሻያ ጋር ተመጋግቦ ሀገሪቱ የፈጠራ ሥራዎች መፍለቂያ (startup nation) እንድትሆን ያደርጋል።

## 1.2. የግብርናው ዘርፍ ያለበት ሁኔታ

ባለፉት የዕቅድ ትግበራ ዓመታት የግብርና ዘርፍ አፈጻጸም አበረታች የነበረ ቢሆንም ዘርፉን በአስተማማኝ ደረጃ ከማዘመን አንጻር ከፍተኛ ክፍተቶች ተስተውለዋል። ከ2003 እስከ 2012 በነበሩት አስር የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የትግበራ ዓመታት የግብርናው ዘርፍ ተጨማሪ እሴት በአማካይ በየዓመቱ በ4.1 በመቶ ሲያድግ ቆይቷል። ይህም በተመሳሳይ ወቅት ከተመዘገበው ከሕዝብ ዕድገት ምጣኔ በላይ በመሆኑ አስቸጋሪ የአየር ንብረት በተከሰተባቸው ዓመታት ዘርፉ ከመፈተኑ በስተቀር በገጠር አማካይ የኑሮ መሻሻል እንዳለ ማስተዋል ይቻላል። ከዚህም በላይ ግብርናው ለሌሎች ዘርፎች ዕድገት መፋጠን የበኩሉን ድርሻ ያበረከተ ሲሆን በተለይም 77 በመቶ ለሚሆነው የሀገሪቱ የሸቀጦች የወጪ ንግድ ገቢ ምንጭ ሆኗል። ይሁን እንጂ ዘርፉ ውስጣዊ መዋቅራዊ ለውጥ

ከማምጣትና ከመዘመን አንጻር አሁንም ከዝናብ ጥገኝነት አለመላቀቁና ለአጠቃላይ መዋቅራዊ ሽግግር አስተዋጽዖ ከማድረግ አኳያ በተለይም ለሌሎች ዘርፎች በቂ ምግብና አስተማማኝ ግብዓቶች ከማቅረብ እንዲሁም ገበያ ከመፍጠር አንጻር የግብርናው ዘርፍ ውስንነት አለበት። የሀገሪቱን ዜጎች የምግብ ፍላጎት ማሟላት ካለመቻሉ በተጨማሪ የዘርፉ የሰው ኃይል ምርታማነትም ዝቅተኛ ነው። የግብርናው ዘርፍ ዕድገት በሚፈለገው ደረጃ ፈጣን እንዳይሆንና የግብርና ትራንስፎርሜሽን እንዳይረጋገጥ ብሎም ለአጠቃላይ ኢኮኖሚው የመዋቅራዊ ሽግግር የተሻለ አስተዋጽኦ እንዳያበረክት የሚገድቡ ማነቆዎች ከቴክኖሎጂ ግብዓት አቅርቦት፣ ከዝቅተኛ የግብርና ኢንቨስትመንት ብሎም ከዝቅተኛ የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም ጋር በተያያዙ በሦስት አበይት ጉዳዮች የሚጠቃለሉ ናቸው። ዋና ዋናዎቹ ተግዳሮቶችም የመስኖ ልማት በተገቢው መጠን አለመስፋፋትና በቴክኖሎጂ ያልታገዘ መሆን፣ የተቀናጀ የግብርና መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሥርዓት አለመኖር፣ ቀጣይነት ያለው የቴክኖሎጂ ማመንጨት፣ የብዜትና ስርፀት ሥርዓት አለመዳበር፣ የግብርና ፋይናንስ እንዲሁም ኢንሹራንስ እና ኢንቨስትመንት በበቂ ሁኔታ አለማደግ፣ የግብርና ግብይት ሥርዓት ዘመናዊ ፍትሐዊና ሕጋዊ ሆኖ ያለመገንባት፣ በግብርና መስክ የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ የሚያበረታታ ሥርዓት አለመኖርና የግብርና ዘርፍ ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም ጋር በተያያዘም የዕውቀት ክህሎትና ተነሳሽነት አነስተኛ መሆን፣ ወጥነት ያለውና የተናበበ አደረጃጀትና አሠራር አለመኖር ተጠቃሽ ናቸው። እነዚህን ተግዳሮቶች ለማሻሻልም ግብርናን ማዘመን አማራጭ የሌለው የዕቅዱ የትኩረት መስክ ተደርጎ ተወስዷል። ዘመናዊ ግብርናም የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ በዘላቂነት ለማሳደግ በቀጣዮቹ አስር ዓመታት ድርብርብ ሚና መጫወት ይጠበቅበታል። ይህም ከፍተኛ ቁጥር ያለውን ሕዝብ መመገብ፣ በመካከለኛ ጊዜ የሚያስፈልገውን የውጭ ምንዛሪ ማስገኘት፣ የመዋቅራዊ ሽግግርን እውን ማድረግ፣ ለኢንዱስትሪውና ሌሎች ዘመናዊ ዘርፎች በቂ ምግብ ግብዓትና የሰው ኃይል ማቅረብ፣ ለሌሎች ዘርፎች ምርቶች ገበያ ወይም ፍላጎት እንዲያድግ የማድረግና የሥራ ዕድል መፍጠር ከግብርናው ዘርፍ በቀጣይ የሚጠበቁ ሚናዎች ናቸው። በመሆኑም ግብርናው እንዲዘምን ከዚህ በላይ የተጠቀሱ ተግዳሮቶች በወሳኝ መልኩ መፈታት ይኖርባቸዋል። ለዚህም በ1994 ዓ.ም ወጥቶ የነበረውን የግብርናና ገጠር ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂ በበለድርሻ አካላት ተሳትፎ እንዲከለስ ተደርጓል። የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱን መልሶ የማደራጀት ስራ የተከናወነ ሲሆን እንደ አረንጓዴ አሻራ፣ የመስኖ ስንዴ እና የሌማት ትሩፋት ያሉ ትልልቅ እቅዶች ትግበራም ተጀምሯል ።

## 1.3. የእንስሳት ዘርፍ ሁኔታ

የእንስሳት ሀብት በኢትዮጵያ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገት ውስጥ ትልቅ ሚና የሚጫወት የግብርና ዘርፍ ነው። ኢትዮጵያ ሰፊ የእንስሳት ቁጥርና ብዝሃ-ህይወት እንዲሁም ለእርባታ ተስማሚ የሆነ የተለያየ ስነ-ምህዳርና የአየር ንብረት ያላት ሲሆን ይህም የእንስሳት እርባታ ለአገሪቱ ኢኮኖሚ እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ለማድረግ ያለውን እምቅ አቅም ያሳያል። በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ዘመን መጨረሻ የእንስሳት ዘርፍ ከአጠቃላይ ሀገራዊ ምርት 8.2 በመቶ ድርሻ እንደነበረው የኢትዮጵያ ፕላን ኮሚሽን መረጃ ያመለክታል ።

የእንስሳት ሀብት ለብዙ አርሶ/አርብቶ አደሮች፣ ከፊል አርብቶ አደሮች እና በርካታ የእንስሳት እሴት ሰንሰለት ተዋናዮች ዋንኛ የኑሮ ዋስትና ነው። ይሁን እንጂ በአብዛኛው የአረባብ ስርዓቱ ያልዘመነና ዝቅተኛ የግብዓት አጠቃቀምና ምርታማነት የሚታይበት በመሆኑ የዘርፉን አዋጭነትና እና የመልማት አቅም እንዲገደብ አድርጎታል። ለዚህም ከሚጠቀሱት ምክንያቶች መካከል የምርት ዓይነትን መሰረት ያደረገ የእንስሳት የኤክስቴንሽን አሰጣጥ ዘዴ አለመኖር፣ የገጠር መሰረተ ልማትና ሜካናይዜሽን አለመሟላት፣ የተሻሻሉ ዝርያዎች እጥረት፣የግል ዘርፉ በእንስሳት ዝርያ ማሻሻል ያለው ተሳትፎ አነስተኛ መሆን ተጠቃሽ ናቸው።

## 1.4. የእንስሳት ልማት ኢንስቲትዩት ሁኔታ

የእንስሳት ልማት ኢንስቲትዩት በአዋጅ ቁጥር 1263 ተቋቁሞ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 506/2014 ስልጣንና ተግባሩ ተወስኗል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 1263 አንቀፅ 105 መሰረት የቀድሞ የብሔራዊ እንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ኢንስቲትዩት እና የቀድሞ የኢትዮጵያ ስጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት መብትና ግዴታዎችም ተላልፈውለታል፡፡ በዚሁ መሰረት ኢንስቲትዩቱ በጥናትና ምርምር፣ ስልጠና እና ማማከር ስራዎች የሚጠበቅበትን ማከናወን በሚያስችል መልኩ በሶስት ዘርፎች የተደራጀ ሲሆን እነዚህም የእንስሳት ዝርያ ማሻሻል ምርምር ዘርፍ፣ የእንስሳት ምርትና መኖ ማቀነባበር ምርምር ዘርፍ እንዲሁም የሶሽዮ ኢኮኖሚክስና እሴት ሰንሰለት አስተዳደር ዘርፍ ናቸው፡፡ በቢሾፍቱና በሆለታ የእንስሳት ልማት ማዕከላት ያሉት ሲሆን ይርጋለም፣ ቡሬ፣ቡልቡላ እና በአከር የተቀናጀ የአግሮ ኢንዱስትሪ ጽ/ቤቶች አሉት፡፡

ኢንስቲትዩቱ የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር መፈጸም የሚያስችለውን ድርጅታዊ መዋቅር አዘጋጅቶ ባስጸደቀው መሰረት ሰራተኞችን ደልድሎ ከመስከረም 1/2015 ዓ.ም ጀምሮ ወደ ስራ ገብቷል፡፡ በዚህም መሰረት በአሁን ጊዜ በአጠቃላይ 722 ሰራተኞች ያሉ ሲሆን ከዚህም ውስጥ 544 ወንዶች እና 178 ሴቶች ናቸው፡፡ ኢንስቲትዩቱ በዋናነት የእንስሳት ዝርያን በማሻሻል ምርታማነትን ማሳደግ፣የተቀነባበረ የእንስሳት ምርትና ተዋጽኦ ጥራትና ምርታማነት ማሳደግ ፣ ኢንቨስትመንት እና ገበያ እንዲስፋፋ የማድረግ ስራዎችን ያከናውናል፡፡

የዝርያ ማሻሻል ስራውንም ለማሳካት የእንስሳት ርቢ ፖሊሲና ስትራቴጂዎች ተቀርጸው ከዚህ ፖሊሲ የሚመነጩ አምስት የዝርያ ማሻሻል ስትራቴጂዎች ተዘጋጅተዋል፡፡ እነዚህም ብሔራዊ የወተት ከብቶች የርቢ ስትራቴጂ፣ ብሔራዊ የስጋ ዳልጋ ከብቶች የርቢ ስትራቴጂ፣ ብሔራዊ የዶሮ ርቢ ስትራቴጂ፣ ብሔራዊ የአነስተኛ አመንዣኪዎች ርቢ ስትራቴጂ እንዲሁም ብሔራዊ የግመል ዝርያ ማሻሻል ስትራቴጂ ተቀርፀዋል፡፡ ከእነዚህ እስትራቴጂዎች በመነሳት ሶስት ፕሮግራሞች የተዘጋጁ ሲሆን እነዚህም አነስተኛ አመንዣክ እንስሳት ርቢ ፕሮግራም፣ የፎገራ የወተት ዳልጋ ከብት እና የሆሮ የዶሮ ዝርያ፣ዶዮ ገና በግ ዝርያ ፕሮግራም ናቸው ፡፡

በተጨማሪም ተቋሙ ጥናትና ምርምር የሚያከናውን ኢንስቲትዩት በመሆኑና ምርምርም በስትራቴጂ መመራት ስላለበት የወተት ምርምርና ልማት ስትራቴጂ፣ የስጋ ዳልጋ ከብቶች ምርምርና ልማት ስትራቴጂ፣ የዶሮ ምርምርና ልማት ስትራቴጂ፣ የአነስተኛ አመንዣኪዎች ምርምርና ልማት ስትራቴጂ እንዲሁም የግመል ምርምርና ልማት ስትራቴጂ ተቀርፀዋል፡፡

## 1.5. የእቅዱ መነሻዎች

### 1.5.1 ኢትዮጵያ አፍሪካዊት የብልፅግና ተምሳሌት (2013-2022) የፌደራል መንግስት የ10 ዓመት የልማት ዕቅድ እንደመነሻ፣

የልማት ዕቅዱ ዓላማ የታለመውን አፍሪካዊት የብልጽግና ተምሳሌት ለመሆን ጉልህ ሚና መጫወት ነው፡፡ በአስር ዓመቱ የልማት ዕቅድ ዘመን የኢኮኖሚውን ምርታማነትና ተወዳዳሪነት በማሳደግ የኢኮኖሚ ዕድገቱ በሂደት በግሉ ዘርፍ ወደሚመራበት በማሸጋገር የኢኮኖሚ ዕድገቱን ለማስቀጠል፣ የተረጋጋ የማክሮ-ኢኮኖሚ ምህዳር ለመፍጠር፣ ድህነትን በሁሉም መገለጫ በተጨባጭ ለመቀነስ፣ ዘላቂና አስተማማኝ የሥራ ዕድል ለመፍጠር በትኩረት የሚሰራ ዕቅድ ነው፡፡ በባለፉት ዓመታት የተመዘገቡ ስኬታማ አፈጻጸሞች እንደተጨማሪ አቅም የሚወሰዱ ሲሆን በዕቅዱ የትግበራ ሂደት የታዩ ክፍተቶችን በማስተካከል ሁሉም የልማት ተሳታፊዎች በመደመር አስተሳሰብና ተግባር የተቀናጁና ተመጋጋቢ የሆኑ የልማት ሥራዎች በላቀ ቁርጠኝነትና ትጋት በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች እንደሚከናወኑ ታሳቢ በማድረግ ለዚህ እስትራቴጂክ እቅድ እንደ መነሻ ተወስደዋል፡፡

### 1.5.2 የግብርና ሚኒስቴር 10 ዓመት መሪ እቅድ እንደ መነሻ

የግብርናው ዘርፍ ስትራቴጂክ አላማ አንዱ የሆነውን ገበያ ተኮር የእንስሳትና ዓሣ ሀብት ምርት ለማሳደግ ዘመናዊ ቴክኖሎጂን የሚጠቀም አርሶና አርብቶ አደር በመገንባትና በገበያ የሚመራ የእንስሳትና አሳ ሀብት ልማት ለማስፋፋት አቅጣጫ ተቀምጧል። በሚቀጥሉት 10 አመታት የእንስሳት እና አሳ ሀብት ልማት ሁለት የምርት እድገት አማራጮች ማለትም (1) ዝቅተኛ ምርታማነትን ማሻሻል እና (2) የምርት ፍላጎት ማለትም ከኢንዱስትሪ መስፋፋት ጋር የሚፈጠር የግብዓት ፍላጎት፣ ለውጪ ምንዛሬ ግኝት እንዲሁም የኢኮኖሚ እድገት ጋር የሚመጡ የእንስሳት ምርት መጠንና አይነት ለውጥ ለማሟላት ትኩረት ተደርጎ ይሰራል። በተለይም የወተት፣ ቀይ ስጋ፣ የዶሮ ሥጋና እንቁላል፣ ዓሣ፣ ማርና የሐር ኩኩባ ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ አቅጣጫ ተቀምጧል። ይህም የአነስተኛ አርሶ/አርብቶ አደር እና ሰፋፊ እንስሳትና አሳ አመራረት ስርዓቶች ላይ ያተኮረ ይሆናል ተብሎ በተቀመጠው መሰረት እንደመነሻ ተወስዷል።

### 1.5.3 የግብርና ሚኒስቴር 10 በ10 ዕቅድ እንደ መነሻ

ከመደበኛው የ10 ዓመት የግብርና ዘርፍ መሪ እቅድ ባሻገር ግብርና ሚኒስቴር በ10 ዓመት ውስጥ 10 የግብርና ምርቶች ቅድሚያ ተሰጥቷቸው በልዩ እቅድ ይተገበራሉ በሚል ተቀምጠዋል። እነዚህም የወተት፣ የቀይ ስጋ፣ የዶሮ እንቁላልና ስጋ እንዲሁም የእንስሳት መኖ ትኩረት የሚሰጣቸው ሲሆን ሁለቱ አስቻይ ጉዳዮች ማለትም መስኖና ሜካናይዜሽን ደግሞ ለልማቱ ወሳኝ ማሳለጫዎች በመሆናቸው ለስትራተጂው እንደመነሻ ተወስዷል።

### 1.5.4 ብሔራዊ የርቢ ፖሊሲና ስትራቴጂ እንደ መነሻ

የእንስሳት ዝርያ ማሻሻል ተግባር ረጅም ጊዜ የሚወስድ እና በስትራቴጂ የሚመራ ሲሆን ዝርያ ከውጭ ሲገባና ከሀገር ውስጥም ወደ ውጭ ሲላክ የዝርያ መበረዝ፣ የዘረመል መሸርሸር እንዳይከሰት፣ ያልተፈለገ በሽታ ከተለያዩ የዘረመል ግብዓቶች ጋር ከውጭ ሀገር ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገባ፣ የእንስሳትዝርያ ማሻሻል በመርህ በህግና በታለመ ስልት እንዲመራ ለማድረግ እንዲሁም የሙያ ማህበራት፣ የአርቢ ማህበራት፣ የወጣቶችና ሴቶች ተሳትፎ ለማጠናከር የወጣው ፖሊሲ እንደመነሻ ተወስዷል።


## 1.6. የባለፉት አሥር ዓመታት ዋና ዋና አፈጻጸሞች

### 1.6.1 የዝርያ ማሻሻያ ግብዓት አቅርቦትና ሥርጭት

በኢንስቲትዩቱ እና አዲስ በተገነቡት አራት ማዕከላት (መቀሌ፣ ነቀምት፣ ሀዋሳ እና ባህርዳር) የዳልጋ ከብት አባለዘር ከ2003 ዓ.ም እስከ 2012 ዓ.ም 13,360,000 ዶዝ አባላዘር ለማምረት ታቅዶ 7,992,165 ዶዝ የተመረተ ሲሆን አፈፃፀሙም 60 % ነው። ለዚህ አነስተኛ አፈፃፀም ዋና ዋና ምክንያቶች መካከል ለአባለዘር ምርት የሚሆኑ ኮርማዎች የሚመረጡባቸው እርባታዎች ውስን መሆን፣ ከውጭ ሀገር ኮርማ ለማስገባት የውጭ ምንዛሬ እጥረት፣ አባለዘርን ለማምረትና የተመረተውን አባለዘር ለመጠበቅ የፈሳሽ ናይትሮጂን አቅርቦት መቆራረጥ፣ በማምረቻ መሳሪያ ጥገና የባለሙያ እጥረት እና አባለዘር ለማምረት የሚያግዙ አላቂ የላቦራቶሪ ዕቃዎች በሀገር ውስጥ የማይገኙ እና ከውጭ ለማስገባት የውጭ ምንዛሪ መጠየቃቸው የሚጠቀሱ ናቸው።


በተመሳሳይ መልኩ ከዚህ ከተመረተው የዳልጋ ከብት አባለዘር ውስጥ 13,014,200 ዶዝ አባለዘር ለተጠቃሚዎች ለማሰራጨት ታቅዶ 7,290,972 ዶዝ (56 %) ማሰራጨት ተችሏል።

የተመረተውን አባለዘር ተደራሽ ለማድረግ የፈሳሽ ናይትሮጂን እጥረት እና የሎጅስቲክ አቅርቦት ውስንነት በሥርጭት ወቅት ያገጠሙ ችግሮች ናቸው።




**ምስል1፡** የአባለዘር ምርት ክንውን በዶዝ (2003-2012)

የመረጃ ምንጭ፡ የኢንስቲትዩት ሪፖርት





**ምስል 2፡** የአባለዘር፡ ሥርጭት፡ በዶዝ (2003-2012ዓ.ም)

የመረጃ ምንጭ፡ የኢንስቲትዩት ሪፖርት

## 1.6.2 ፈሳሽ ናይትሮጂን ምርትና ሥርጭት


በኢንስቲትዩቱ ሁለት እና በክልሎች ሃያ በአጠቃላይ ሃያ ሁለት የፈሳሽ ናይትሮጅን ማምረቻ መሳሪያዎች ተተክለው በግብዓትነት የሚውሉ የፈሳሽ ናይትሮጂን እያተመረቱ ይገኛሉ፡፡ ባለፉት አስር ዓመታት በኢንስቲትዩቱ እና በክልል የፈሳሽ ናይትሮጂን ማምረቻ ማዕከላት 5,156,160 ሊትር ለማምረት ታቅዶ 3,071,492 ሊትር የተመረተ ሲሆን አፈፃፀሙም 60% ነው፡፡ ለዚህም አነስተኛ አፈፃፀም በፈሳሽ ናይትሮጂን ማምረቻ ማሳሪያዎች የጥገና የባለሙያና የመለዋወጫ እጥረት እንዲሁም የዋጋ ውድነት ዋነኛ ምክንያቶች ናቸው፡፡

በተመሳሳይ መልኩ ከተመረተው የዳልጋ ከብት አባለዘር ውስጥ 3,662,754 ሊትር ፈሳሽ ናይትሮጂን ለተጠቃሚዎች ለማሰራጨት ታቅዶ 2,282,653 ሊትር (62%) ተሰራጭቷል፡፡ የተመረተውን ፈሳሽ ናይትሮጂን በአግባቡ ሥራ ላይ ለማዋል፣ ለሥራ አስፈላጊ በጀትና የሎጀስቲክ አቅርቦት በወቅቱ ባለመሟላቱ በበቂ ሁኔታ ማሰራጨት አልተቻለም፡፡




**ምስል 3፡** የፈሳሽ ናይትሮጅን ምርት (2003-2012 ዓ.ም)

ምንጭ፡ የኢንስቲትዩቱ ሪፖርት




**ምስል 4፡** የፈሳሽ ናይትሮጅን ምርት (2003-2012 ዓ.ም)

ምንጭ፡ የኢንስቲትዩቱ ሪፖርት

## የአዳቃይ ቴክኒሽንና የፈሳሽ ናይትሮጅን ማምረቻ መሳሪያ ኦፕሬተሮች ሥልጠና

አብዛኛዎቹ በአርሶ አደሩና በአርብቶ አደሩ እጅ ያሉት እንስሳት በምርታማነታቸው ዝቅተኛ የሆኑ የሀገር በቀል ዝርያዎች በመሆናቸው በተጠና መንገድ ዝርያን ማሻሻል ወሳኝ ነው፡፡ የአገር በቀል የዳልጋ ከብት የወተት ምርት በቀን ከ2 ሊትር የማይበልጥ ስለሆነ እነዚህን እንስሳት ምርታማ ከሆኑ የውጪ ዝርያዎች ጋር በማዳቀል ምርታማነታቸውን ለማሻሻል ኢንስቲትዩቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እየሰራ ነው፡፡

የእንስሳት ዝርያን በመረጣና በሰው ሰራሽ ዘዴ ለማሻሻል የሰለጠነ የሰው ኃይል ማፍራት ዋና ተግባር ስለሆነ ቴክኖሎጂውን ተደራሽ የሚያደርጉ ባለሙያዎች የማሰልጠን ሥራ ኢንስቲትዩቱ በተለያዩ ስያሜዎችና አደረጃጀቶች

ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ላለፉት ዓመታት ሲያከናውን ቆይቷል። የሰው ሰራሽ እንስሳት ማዳቀል ሥራ ፍላጎት በአርቢው ማህበረሰብ ዘንድ እየታወቀና ፍላጎቱም እየጨመረ መጥቷል። በዚህም ባለፉት አሥርት ዓመታት (2003-2012 ዓ.ም) ብቻ ኢንስቲትዩቱ ለ 40 የአዳቃይ ቴክኒሽኖች አሰልጣኞች ሥልጠና፣ ለ 898 ለአዳዲስ አዳቃይ ቴክኒሽኖች ሥልጠና፣ ለ 467 ሥራ ላይ ላሉ አዳቃይ ቴክኒሽኖች የተሐድሶ ሥልጠና፣ የአባላዘር መሳሪያዎች ጥገናና አጠቃቀም እንዲሁም የላቡራቶሪ መሳሪያዎች አሰራር ቅድም ተከተል ለ15 ሰራተኞች በአምስት ዙር እና ለ 11 የፈሳሽ ናይትሮጅን መሳሪያ ኦፕሬተሮች በተለያየ ዙር ሥልጠና ተሰጥቷቸዋል።

## የተሻሻሉ የእንስሳት ዝርያዎች እና ስርጭት

ለአባለዘር ምርት የሚውሉ የተመረጡ ኮርማዎችን ወደ አባለዘር ማምረቻ ማዕከላት  በማስገባት ረገድ ባለፉት አስር 10 አመታት 269 ታዳጊ ኮርማዎች ከሀገር ውስጥና ከውጭ ሀገር ማስገባት ተችሏል። በእነዚህ ኮርማዎች ላይ የመራቦ አካል እና የማስረገዝ ብቃት ፍተሻ ተካሄዶ ብቁ ሆነው የተገኙት 240 ኮርማዎች ባለፉት አስር ዓመታት ለምርት አገልግሎት ዝግጁ ተደርገዋል። በተመሳሳይ የተመረጡ አውራ በጎች እና ፍየሎችን ከክልሎች ጋር በመቀናጀት የማሰራጨት ስራ እየተሰራ ሲሆን ባለፉት ሶስት አመታት የተመረጡ 34,981 አውራ በጎች እና 10,054 አውራ ፍየሎችን በማሰራጨት በዘርፉ የተሻሻሉ ዝርያዎችን በማሳደግ የአርሶ/አርብቶ አደሩን ተጠቃሚነት ለማሳደግ ጥረት ተደርጓል። እስከ አሁን በተሰሩ የዝርያ ማሻሻል ስራዎች የተሻሻሉ ዝርያዎች ድርሻ በመቶኛ ሲታይ የዳልጋ ከብት 3.54%፣ የተመረጡ የበግ ዝርያዎች 0.52%፣ የተመረጡ የፍየል ዝርያዎች 0.16%፣ የተሻሻሉ የዶሮ ዝርያዎች 26% ቢሆንም አገሪቱ ካላት የስነ-ምህዳር ዕምቅ አቅም አንፃር የዝርያ ማሻሻሉ ስራ ገና ያልተነካ ነው ማለት ይቻላል። በተለይ ግመልን ጨምሮ የተሻሻሉ  የሥጋ የዳልጋ  ከብት ፣ የዓሳ እና የንብ ህብረ-መንጋ ስርጭት ላይ በትኩረት በመስራት የዘርፉን ምረታመነት በማሻሻል የህዝቡን ተጠቃሚነት ለማሳደግ በትኩረት መስራት ያስፈልጋል። በባለፉት ሶስት ዓመታት የተሻሻሉ ዝርያዎች ተጠቃሚ የሆኑ አርሶ/አርብቶ አደሮች 12% ማሳደግ የተቻለ ቢሆንም በተሰራጩ የተሻሻሉ ዝርያዎች ዓይነት ሲታይ በአንዳንድ ዝርያዎች ተደራሽነቱ ዝቅተኛ ነው። ስለሆነም የአርሶ/አርብቶ አደሮች ከዘርፉ የሚያገኙትን ገቢ ለማሻሻል እና የህዝቡን ተጠቃሚነት ለማሳደግ በሁሉም የተሻሻሉ ዝርያዎች ተደራሽነትን ለማረጋገጥ ከሚመለከተው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መስራት በጣም አስፈላጊ ነው።

## የዝርያ ማሻሻል ብዜት ማዕከላት

በእንስሳት ዝርያ ማሻሻል ሂደት ውስጥ የዝርያ ማሻሻል ብዜት ማዕከላት የማይተካ ሚና ያላቸው መሆኑ ይታወቃል። ባለፉት ሶስት ዓመታት 4 ነባር የዝርያ ማሻሻል የብዜት ማዕከላትን በመደገፍ እና በማጠናከር እንዲሁም 3 አዲስ ማዕከላትን በማቋቋም ስራ ማስጀመር ተችሏል። በነባር እና አዳዲስ ብዜት ማዕከላት 400 የተመረጡ የቦረና ጊደሮች እና 1304 የፎገራ ዝርዎችን በማስገባት ፆታው በተለየ አባለዘር እንዲጠቁ በማድረግ 50% የደም መጠን ያላቸው 188 እንስት ጥጃዎችን ማግኘት ተችሏል። ይህ ጅምር ስራ የዘርፉን የምርምር ስራ የሚያሻሽል ሲሆን በማዕከላት የሚባዙ ዝርያቸው የተሻሻሉ ጊደሮችን ለአርሶ/አርብቶ አደሩ በማሰራጨት ምርት እና ምርታማነትን ለማሳደግ በትኩረት የሚሰራ ይሆናል።

## የእንስሳት ዝርያ ኢንፎርሜሽን ማሳደግ

በእንስሳት ምርታማነት ምዝገባና ግብረ-መልስ የእንስሳት ምርታማነትን ከማሳደግ አኳያ በሉኬ (Luke- የፊንላንድ ድርጅት) እና African Dairy Genetic Gain DGG ፕሮጀክቶች ድጋፍ በርካታ ሥራዎችን ለማከናወን የታቀደ ሲሆን በተለይም በዋናነት እስከ 2012 ዓ.ም  74 መረጃ መዝጋቢዎች በፕሮጀክቶቹ በኮንትራት ተቀጥረው 13,800 አዲስ እርባታዎችን  በመመዝገብ ወደ መረጃ ቋት አስገብተዋል። በተጨማሪም 60,000 የወተት ምርታማነት ምዝገባ በማካሄድ ወደ መረጃ ቋት በማስገባት በመረጃ ቋት ለተመዘገበላቸው አርብቶ/አርሶ አደር መረጃውን በመተንተን

እንዲሁም አጠቃላይ ምክረ ሀሳብ ስለ ወተት ከብት እርባታ አያያዝና እንክብካቤ በሞባይል 150 አጭር የጹሁፍ መልዕክት (ግብረ-መልስ) ለተመዘገቡ አርቢዎች ተደራሽ ተደርጓል።

### 1.6.3 የእንስሳት ምርትና መኖ ማቀነባበር አፈጻጸም ግምገማ


በኢትዮጵያ የእንስሳት ምርትና መኖ ማቀነባበሪያዎችን በመደገፍ ፈጣንና ቀልጣፋ የኢኮኖሚ ዕድገትን ለማረጋገጥ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳለው ይታመናል። የእንስሳት ምርትና መኖ ማቀነባበሪያዎች በጥናትና ምርምር፣ በገበያ ትስስር፣ የአቅም ግንባታ ስልጠናና የቴክኒክ ድጋፎችን በመስጠት ምርቶቻቸውን ወደ ውጪ ሀገራት ልከው የውጪ ምንዛሪ እንዲያስገኙና የገቢ ምርቶችን በመተካት የውጪ ምንዛሪ ለማዳን እንዲሁም ለዜጎች በተለይም ለወጣቶችና ሴቶች የስራ ዕድል እንዲፈጠር ባለፉት የዕቅድ ትግበራ ዓመታት በርካታ ጥረቶች ተደርገዋል።ይሁንና ካለው እምቅ የእንስሳት ሀብት አንፃር የእንስሳት ምርትና መኖ ማቀነባበሪያዎች ለኢኮኖሚው እያበረከቱ ያለው አስተዋፅኦ እጅግ ዝቅተኛ ነው።


### 1.6.4 የወጪ ንግድ እና ተኪ ምርቶች አፈጻጸም

የወጪ ንግድ ገቢን በተመለከተ ከ2003-2012 ባሉት አስር አመታት 448,849.18 ቶን የሥጋ፣ የማርና ሰም እና 16,180 ሚሊዮን ሊትር ወተት በመላክ 1,779.55 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ በቅደም ተከተል 192,522.50 ቶን (42.89%)፣ 18,224 ሚሊዮን ሊትር (112.63%) ወተት ተልኮ 902.33 ሚሊዮን (50.71%) የአሜሪካን ዶላር ገቢ ተገኝቷል። ለዚህ አፈፃፀም ዝቅተኛ መሆን ከሚጠቀሱ ምክንያቶች መካከል የእርድ እንስሳት እና የማር ምርት አቅርቦት በጥራትም ሆነ በመጠን ዝቅተኛ መሆን፣ የተቀባይ አገራትን ፍላጎት ማሟላት ያለመቻል፣ የገበያ ውስንነት፣ የቁም እንስሳት ህገ ወጥ ንግድ መስፋፋት፣ የአገር ውስጥ የእንስሳትና የእንስሳት ውጤቶች ዋጋ መናር ዋንኞቹ ናቸው።

### 1.6.5 የሥጋና የእርድ ተረፈ-ምርት አፈፃፀም

የኤክስፖርት ቄራዎች የማምረት አቅም ከዛሬ አስር ዓመት በፊት ከነበረው ዓመታዊ የማምረት አቅም ጋር ሲነፃፀር እጅግ ከፍተኛ የሚባል ዕድገት (559%) አሳይቷል (ከ30,380 ቶን ወደ 200,300 ቶን)። ሆኖም ግን ባለፉት ዓመታት ማቀነባበሪያዎች አማካይ ዓመታዊ የማምረት አቅም አጠቃቀማቸው ከ20 ሺህ ቶን አላለፈም። የወጪ ንግድ አፈፃፀሙ ባለፉት አስር ዓመታት በተለይም ከ2000 በጀት ዓመት እስከ 2010 በጀት ዓመት ተከታታይነት ያለው ዕድገት እያስመዘገበ የመጣ ቢሆንም በመጨረሻዎቹ ተከታታይ ሁለት ዓመታት (2011 እና 2012) ቅናሽ አሳይቷል። ዋና ምክንያቶቹም የቁም እንስሳት አቅርቦት እጥረትና ከፍተኛ ዋጋ ናቸው።





ምስል5: የሥጋና ዕርድ ተረፈ-ምርት አፈፃፀም (2003 - 2012 ዓ.ም)
ምንጭ: የጉሙሩክ የወጪ ንግድ የመረጃ ቋት.


### 1.6.6 የማርና ሰም የወጪ ንግድ አፈፃፀም

በአንደኛው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን 5641 ቶን ማርና ሰም አቀነባብሮ ወደ ለውጪ ገበያ በማቅረብ 26.773 ሚሊዮን ዶላር ገቢ ተገኝቷል፡፡ በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን 6.72 ሺህ ቶን ማርና 2.37 ሺህ ቶን ሰም አቀነባብሮ ወደ ውጭ ገበያ በመላክ 28.84 እና 26.48 ሚሊዮን ዶላር በቅደም ተከተል ገቢ ለማግኘት ታቅዶ ሲሰራ የቆየ ቢሆንም አፈፃፀሙ በጣም አናሳ ነው፡፡

የተቀነባበረ ማርና ሰም ምርት ኤክስፖርትን በተመለከተ በአንደኛው የዕድገትና ራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን 2,326 ቶን የማርና ሰም ምርትን ኤክስፖርት ለማድረግ በዕቅድ ተይዞ የነበረ ሲሆን በዚሁ መሰረት 5,793 (ማር 3,959 እና ሰም 1,834) ቶን ወይም የዕቅዱን 168 በመቶ የማርና ሰም ምርት ኤክስፖርት በማድረግ በድምሩ 26.09 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የወጪ ንግድ ገቢ ተገኝቷል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ 4588.92 ቶን ማርና 3051.36 ቶን ሰም ወደ ውጪ በመላክ 13.58 እና 26.97 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር በቅደም ተከተል ለማግኘት ታቅዶ 1634.48 (35.62%) ቶን ማርና 1412.16 (46.29%) ቶን ሰም ወደ ውጭ በመላክ 5.34 (39.32%) እና 12.39(45.94%) የአሜሪካን ዶላር ገቢ ተገኝቷል፡፡

በማርና ሰም ምርት ማቀነባበርና ወጪ ንግድ የተሰማሩ የግል ድርጅቶች፤ማህበራቶች እና ዩኒየኖች የሚገኙ ሲሆን በማር ማቀነባበርና ንግድ 20 የሚሆኑ ካምፓኒዎች እንዲሁም በሰም ማቀነባበርና ንግድ 5 የሚሆኑ ካምፓኒዎች በድምሩ 25 የሚሆኑ ካምፓኒዎች በንዑስ ዘርፉ ምርት ማቀነባበርና ንግድ ተሰማርተው አስፈላጊው ድጋፍ እየተደረገላቸው የሚገኝ ሲሆን ሌሎች በጥቃቅንና አነስተኛ መጠን ማርና ሰምን በማቀነባበር ንግድ የተሰማሩ ኢንተርፕራዞችም በየክልሉ በስራ ላይ ይገኛሉ፡፡








**ምስል 7፡** የሰም ምርት የወጪ ንግድ አፈጻጸም (ከ2003 - 2012 ዓ.ም)
**ምንጭ፡** የጉሙሩክ የወጪ ንግድ የመረጃ ቋት

### 1.6.7 የዓሣ ሥጋ የወጪ ንግድ አፈፃፀም

የዓሳ ሥጋ ማቀነባበር በሚፈለገዉ ደረጃ ላይ የሚገኝ ባይሆንም መጠነኛ እሴት በመጨመር ለውጭ ገበያ እየቀረበ ይገኛል፡፡ ከዚህ ማቀነባበሪያ የሚገኘዉ የዉጪ ምንዛሪ እጅግ በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ ካለን የውሃ ሐብት እና እየተገነቡ ካሉት ግድቦች አንፃር ለዓሣ ሐብት ልማት በርካታ ዕድሎች ያሉን ቢሆንም ማቀነባበሪያዎች በሚያስገኘው ገቢ፣ በሚፈጥረዉ የሥራ ዕድል፤ የሚፈጠረው የቴክኖሎጂ ሽግግር፣ በሚጨምረው እሴት እና በመሰል መመዘኛዎች እየተገኘ ያለዉ ሀገራዊ ጥቅም በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የዓሣ ምርት የወጪ ንግድ በአንፃራዊነት በአንደኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽ እቅድ ዘመን የተሻለ አፈፃፀም የነበረው ቢሆንም በሁለተኛ የእድገትና ትራንስፎርሜሽ እቅድ ዘመን አፈፃፀሙ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ መጥቷል፡፡ በአንደኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽ እቅድ ዘመን 4185.67 ቶን አሣ ተልኮ 2.11 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ተገኝቷል፡፡ በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ዘመንም 3856.3 ቶን አሣ በመላክ 1.87 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ለማግኘት ታቅዶ 1961.63 (50.87%) ቶን በመላክ 0.82 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር (43.75%) ገቢ ተገኝቷል፡፡





**ምስል 8፡** የዓሣ ሥጋ ምርት የወጪ ንግድ አፈጻጸም (2003-2012 ዓ.ም)
**ምንጭ፡** የጉምሩክ የወጪ ንግድ የመረጃ ቋት

### 1.6.8 የዶሮ ስጋ ምርት አፈፃፀም

ሁለት ደረጃቸውን የጠበቁ በቀን እያንዳንዳቸው 5 ሺህ ዶሮዎችን ማረድ የሚችሉና መሰረታዊ የዶሮ ስጋ ማምረቻ መሳሪያዎች ኖሯቸው እያንዳንዳቸው 1000 ዶሮዎችን በቀን ማረድ የሚችሉ ድርጀቶች ወደ ስራ እንዲገቡ ተደርጓል፡፡ በስራ ላይ የነበሩትና በአዲስ መልክ ስራ የጀመሩት የዶሮ ስጋ ማቀነባበሪያዎች ጥራቱን የጠበቀ ምርት ለገበያ እንዲቀርቡ በታቀደው መሠረት የሙያ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ከ2008-2012 በድምሩ 8,029.25 ቶን የዶሮ ስጋ ተመርቶ ለሀገር ውስጥ ገበያ ቀርቧል፡፡

በ2008 በጀት ዓመት ተመርቶ ለሀገር ዉስጥ ገበያ የቀረበው 1379 ቶን የዶሮ ስጋ ምርት በ2012 በጀት ዓመት ከአምስት የዶሮ ስጋ አምራች ድርጅቶች 27 በመቶ ከፍ ብሎ 1752 ቶን የዶሮ ስጋ ምርት ተመርቶ ለሀገር ውስጥ ገበያ ቀርቧል፡፡




**ምስል 9፡** ተመርቶ ለሀገር ውስጥ ገበያ የቀረበው የዶሮ ሥጋ ምርት (2008 - 2012 ዓ.ም)
**ምንጭ፡** የኢንስቲትዩቱ ሪፖርት

### 1.6.9 የእንስሳት መኖ ምርት አፈፃፀም


በሀገር ደረጃ ከአምስት ዓመት በፊት ከአሥር የማይበልጡ የተመጣጠነ የእንስሳት መኖ ማቀነባበሪያ ድርጅቶች የነበሩ ሲሆን በተፈጠረላቸው ምቹ ሁኔታ በአሁኑ ወቅት 60 በላይ መኖ ማቀነባበሪያዎች አሉ። ከእነኚህም መካከል ከፍተኛ የማምረት አቅም ያላቸውና ደረጃውን የጠበቀ ቴክኖሎጂ የሚጠቀሙ ድርጅቶችም ተፈጥረዋል። በተቀነባበረ መኖ በቂ ግንዛቤ ባለመኖሩና ከዋጋቸውም ውድነት የተነሳ ለእንስሳት መኖነት የማዋል ልምድ ውስንነት የነበረ ቢሆንም ፍላጎቱ እየጨመረና እንስሳትን የመመገብ ልምዱ እየዳበረ መጥቷል። በ2008 በጀት ዓመት በአምስት የግልና 14 ዩኒየኖች መኖ ማቀነባበሪያዎች ተመርቶ ለገበያ የቀረበው 376,007 ኩንታል መኖ ምርት በ2012 በጀት ዓመት በስምንት የግልና 13 ዩኒየኖች መኖ ማቀነባበሪያዎች በ976,313 ኩንታል ወይም በ3.6 እጥፍ ጨምሮ 1,352,320 ኩንታል የተቀነባበረ መኖ ምርት ለሀገር ውስጥ ገበያ ቀርቧል።




**ምስል 10፡** ተቀነባብሮ ለሀገር ዉስጥ ገበያ የቀረበ የእንስሳት መኖ (ከ2008 - 2012 ዓ.ም)
**ምንጭ፡** የኢንስቲትዩቱ ሪፖርት


### 1.6.10. የወተትና የወተት ምርት ማቀነባበር አፈጻጸም

በሃገራችን ውስጥ የሚገኙ 35 የወተትና ወተት ተዋጽኦ አምራች ማቀነባበሪዎች ጥሬ ወተትን በግብዓትነት በመጠቀም ልዩ ልዩ የወተት ውጤቶችን በማቀነባበር የወተት ፊዚኮ ኬሚካል ትንተና እና ማይክሮባዮሎጂካል ፍተሻ አገልግሎት በመስጠት ጥራት ያለው የተቀነባበረ ወተት እንዲመረት ድጋፍ ተደርጓል፡፡ በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ትግበራ ዘመን በወተት ማቀነባበሪዎች 574.85 ሚሊዮን ሊትር ወተት ለማቀነባበር በእቅድ የተቀመጠ ሲሆን 457.43 ሚሊዮን ሊትር ወተት በማቀነባበር ለሀገር ውስጥ ገበያ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም ተኪ ምርቶች ላይ በትኩረት በመስራት ከውጪ ከሚገባው ምርት ጋር ተወዳዳሪ የሆነ ፓስቸራይዝድ ወተት ለኢትዮጵያ አየር መንገድ በማቅረብ በ2012 በጀት ዓመት ብቻ 160,330.909 የአሜሪካን ዶላር ወጪን ማስቀረት ተችሏል፡፡ በሌላ መልኩ ለወተት ምርት አገልግሎት ከውጪ ይገባ የነበረውን የወተት ማሸጊያ በሀገር ውስጥ አምርቶ ለወተት ፋብሪካዎች በማቅረብ 1,930,384.85 የአሜሪካን ዶላር ወጪ ማስቀረት ተችሏል፡፡




**ምስል 11፡** በሀገር ውስጥተቀነባብሮ ለገበያ የቀረበ ወተትና የወተት ተዋፅዖ ምርት (ከ2008-2012 በጀት ዓመት)
**ምንጭ:-** ከዓመታዊ የስጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ሪፖርት

የግመል ወተት ምርትን እሴት ከመጨመር አንጻር በርካታ ስራዎች የተከናወኑ ቢሆንም የሚፈለገውን የጥራት ደረጃ ላይ ሙሉ ለሙሉ መድረስ አልተቻለም፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የወጪ ንግድ ወደ አጎራባች ሃገራት (ጅቡቲና ሶማሊያ) በአንደኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽ እቅድ ዘመን 9.86 ሚሊዮን ሊትር የግመል ወተት የተላከ ሲሆን 0.98 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ማግኘት ተችሏል፡፡ በሁለተኛዉ የእድገትና ትራንስፎርሜሽ እቅድ ዘመን ደግሞ 8.36 ሚሊዮን ሊትር የግመል ወተት ተልኮ 1.01 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ተገኝቷል፡፡ በአንፃራዊነት በአንደኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽ እቅድ ዘመን በመጠን የተሻለ ምርት የተላከ ሲሆን በገቢ ደረጃ ግን የሁለተኛ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽ እቅድ ዘመን የተሻለ መሆኑን ያሳያል፡፡ ይህም የምርት ዋጋ በከፍተኛ መጠን እየጨመረ መሄዱን ጠቋሚ ነው፡፡




**ምስል 12፡** የወተትና ወተት ተዋፅዖ የወጪ ንግድ አፈጻጸም (ከ2003-2012 ዓ.ም)

**ምንጭ:-** ከኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን የወጪ ንግድ የመረጃ ቋት

# 1.7. ዋና ዋና የድጋፍ ስራዎች አፈጻጸም

## 1.7.1 የግብይት ሥራዎች

ነባር የሥጋ መዳረሻ ገበያዎች የሚስፋፉበትንና አዳዲስ ገበያዎች የሚፈጠሩበትን ስልት ለመቀየስ እና በገበያ ሂደት ውስጥ ለሚያጋጥሙ ችግሮች በጥናት የተደገፈ መፍትሄ የመስጠት ስራዎች የተለየ ትኩረት በመስጠት ሲሰሩ የቆዩ ተግባራት ቢሆኑም የሚጠበቀውን የኤክስፖርት ዕቅድ ከማሳካት አኳያ ብዙ ይቀረዋል። ሆኖም የሥጋ አምራችና ላኪዎች ምርታቸውን ለማስተዋወቅና ደንበኞችን ለማፍራት እንዲችሉ በሀገር ውስጥና በውጪ በሚካሄዱት ትርዒቶች እና ኢግዚብሽኖች ላይ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ባለሀብቶች እንዲሳተፉ ተደርጓል። በዋናነትም በየዓመቱ የሚካሄደው የምግብ እና ምግብ-ነክ ዓለም አቀፍ ኢግዚብሽንና የንግድ ትሪኢቶች ላይ ባለሀብቶችን በማሳተፍ ምርቶቻቸውን እንዲያስተዋውቁ እና በገበያ እንዲተሳሰሩ የማድረግ ድጋፍ ተደርጓል። ሳውዲ አረቢያና የተባበሩት አረብ ኢሜሬትስ የሚገኙ ደንበኞችን በመለየት እና ከኤክስፖርት ቄራዎች ጋር በማስተሳሰር የተሻለ ዋጋ ለማግኘት በተያዘው ዕቅድ መሰረት በዱባይ ዓለም አቀፍ የምግብ ኤግዚብሽን ላይ ሁሉም የሥጋ ኤክስፖርት ቄራዎች እና የተመረጡ የቁም እንስሳት ላኪዎች እንዲሳተፉ ተደርጓል።

የእርድ እንስሳት አቅርቦት ችግር ለመፍታት የግል ባለሀብቶችና የቄራ ባለቤቶች መሬት ወስደው የዳልጋ ከብት፣ በግና ፍየል እንዲያረቡና እንዲያደልቡ ብሎም ከይዞታቸው ለእርድ እንዲያቀርቡ በተቀመጠው አቅጣጫ መሠረት የእንስሳት እርባታ (ራንች) ለማቋቋም ታቅዶ ሉና የራንች ኢንቨስትመንት ቦታ ወስዶ ማልማት ጀምሯል።

በሌላ በኩል በግብዓት አቅርቦት ያጋጠሙ እና ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችን ለመፍታት ዘርፉን እየደገፉ ካሉት መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በእሴት ሰንሰለቱ የሚሳተፉት አካላት ጤናማ የሆነ ግንኙነት በመፍጠር የግብዓት አቅርቦት ችግሮችን ለመቅረፍ በርካታ ጥረቶች ተደርገዋል። ከዚህ በተጨማሪ በዘርፉ የሚታዩ የግብይት ችግሮችን ለመፍታት የወተት፣ የማርና ሰም ጥራትና ግብይት ረቂቅ አዋጅ ተዘጋጅቶ፣ አዋጁን የማፀደቅ ሥራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ።

### 1.7.2 የአቅም ግንባታ ሰልጠና እና የቴክኒክ ድጋፍ ስራዎች

በእንስሳት ምርትና መኖ ማቀነባበሪዎች የሥልጠና ፍላጎት ዳሰሳ በማድረግ የሠራተኞች ዕውቀትና ክህሎትን በማሳደግና በማሻሻል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ባለፉት ዓመታት ኢንስቲትዩቱ በርካታ ሥልጠናዎችን ሰጥቷል፡፡

በሥጋና ተረፈ ምርተ ማቀነባበሪያዎች በሃይጅንና ሳኒቴሽን፣ በሥጋ አበላለት፣ በዘመናዊ እርድ፣ በስጋ ቀዝቃዛ ሰንሰለት አጠባበቅ፣ በሃላል ሥርዓት፣ በተረፈ ምርት አያያዝና አጠቃቀም፣ በእንስሳት አቅርቦትና ግብይት ለ 3128 (2290 ወንድ እና 838 ሴት) ሰልጣኞች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

በወተት ማቀናበርና ፓኬጂንግ በወተት ጥራት ቁጥጥር፣ የተለያዩ የወተት ውጤቶችን (ዩጎርት፣ ቺዝ፣ ክሬምና ቅቤ) አመራረት፣ በንጹህ ወተት አመራረትና አያያዝ፣በግብዓት አጠቃቀም፣ በቆሻሻ አወጋገድ፣ በወተት ማሽኒያዎች መልሶ አጠቃቀም ለ 2033 (1679 ወንድ እና 354 ሴት) ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ በመኖ ማቀነባበሪያዎችና ዩኒየኖች በተሻሻሉ ዘመናዊ የመኖ አመራረት ለ 89 ( 59 ወንድና 30 ሴት) ሰልጣኞች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ በአጠቃላይ ለ 5250 (4028 ወንድና 1222 ሴት) የእንስሳት ምርትና መኖ ማቀነባበሪያዎች እና ባለድርሻ አካላት ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

### 1.7.3 የጥናትና ምርምር ሥራዎች

ኢንስቲትዩቱ ከተሰጡት ተግባርና ኃላፊነቶች መካከል አንዱ የተለያዩ ጥናትና ችግር ፈቺ ምርምሮችን በማካሄድና ተደራሽ በማድረግ የንዑስ ዘርፉን ማነቆዎች በመቅረፍ ምርትና ምርታማነትን በማሻሻል በገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆን ማስቻል ሲሆን ይህንንም ለማሳካት በዕቅድ ዘመኑ የተለያዩ ጥረቶች ተደርገዋል፡፡

ባለፉት አምስት አመታት በእንስሳት ምርትና መኖ ማቀነባበር 10 እንዲሁም የአከባቢ ብክለት ቅነሳ አንድ የጥናትና ምርምር ስራን ጨምሮ 11 የጥናትና ምርምር ሥራዎች ለህትመት በቅተዋል፡፡

በንዑስ ዘርፉ የሚስተዋሉ ችግሮችን በመፍታት ረገድ የሚካሄዱ ምርምሮች በጅምር ደረጃ ያሉ ሲሆን ለዚህም ዋንኛ ምክኒያቶቹ የምርምር መሰረተ-ልማት ያለመሟላት፣ ልምድ ያላቸው ተመራማሪዎች ያለመኖር፣ ዘርፉ በሚፈልገው መስክ እና ደረጃ ባለሙያዎችን ማስተማርና ማሰልጠን ያለመቻሉ እና ተመራማሪዎችን የሚያበረታታ ስርአትን ተግባራዊ ያለማድረግ ናቸው፡፡ ስለሆነም እነኚህን ችግሮች በመቅረፍ ችግር ፈቺ ምርምሮችን በቀጣይ የዕቅድ ዘመናት ለማካሄድ አስፈላጊው ዝግጅቶች መደረግ ይኖርባቸዋል፡፡

### 1.7.4 የኢንቨስትመንት የድጋፍ ስራዎች

በዕቅድ ዘመኑ አዳዲስ ባለሀብቶች በንዑስ ዘርፉ ኢንቨስትመንት እንዲሰማሩ ጥረቶች የተደረጉ ሲሆን የውጮም ሆነ የሀገር ውስጥ ባለሀብትን ለመሳብም የተለያዩ የንግድ ትርዒቶች ላይ በመሳተፍ፣ በዘርፉ ዓለም አቀፍ ኤግዚብሽን በማዘጋጀት የሀገሪቱን ገጽታ እና ምቹ ሁኔታዎችን በዓለም ለማስተዋወቅ በተደረገው ጥረት ጥቂት የማይባሉ ባለሀብቶች በዘርፉ ገብተው እያለሙ ይገኛል፡፡ በዚሁ መሠረት ባለፉት አምስት ዓመታት በጠቅላላው ሰባት የኤክስፖርት ቄራዎች እና ሁለት የእርድ ተረፈ ምርት ማቀነባበሪያ በድምሩ ዘጠኝ አዳዲስ ኢንቨስትመንቶች በሥጋና እርድ ተረፈ ምርት ማቀነባበር እንዲሰማሩ ማድረግ የተቻለ ሲሆን ከነዚህም ቄራዎች ሦስቱ የፕሮጀክት ጊዜያቸውን አጠናቀው ወደ ምርት የገቡ ሲሆን ቀሪዎቹ በግንባታ ሂደት ላይ ይገኛሉ፡፡

ባለፉት አምስት ዓመታት በፕሮጀክት ደረጃ ያሉ ስድስት አዳዲስ ኢንቨስትመንቶችን ወደ ምርት ማሸጋገር ተችሏል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በሀገሪቷ ሦስት ክልሎች (ኦሮሚያ፣ ደቡብና ትግራይ) እየተገነቡ ባሉት የአግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ በእንስሳት ምርትና መኖ ማቀናበር የሚሰማሩ ባለሐብቶች እንዲገቡ እየተሰራ ባለው ስራ በትግራይ

ክልል ሦስት፤ በደቡብ ክልል ሁለት እንዲሁም በኦሮሚያ ሦስት ባለሀብቶች ተመዝግበዋል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ 11 የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ሲሆኑ ቀሪዎቹ የውጭ ባለሀብቶች ናቸው፡፡

ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ለኢንቨስትመንት የሚውል የመሬት፣ የባንክ ብድር፣ የመብራትና የውሃ መሠረተ ልማት፣ አስፈላጊ የሆኑ ማሽነሪዎች እና ከልድ ትራክ መኪኖች ከቀረጥ ነጻ ታሪፍ ድጋፍ፣ የወጪ መጋራትና ከውጭ ባለሙያዎችን ከማስገባት ሥራ ጋር በተገናኘ ለ13 የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ክትትልና ድጋፍ ተደርጓል፡፡

### 1.7.5 የግንባታ እና ኢንጂነሪንግ ድጋፍ፡ የተቀናጀ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርኮች

የግብርና እና የተፈጥሮ ሃብት በአግባቡ ለመጠቀም የግብርና ዘርፉን ማዘመንና ከማንፋክቸሪንግ ጋር ዘላቂና ጠንካራ የሆነ ትስስር ተሰርቶ የተቀናጀ የአግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክ 17 የልማት ቀጠናዎች በአገሪቱ ክልሎች የተመረጡ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በአራት ክልሎች በኦሮሚያ፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች፣ በአማራ እና ትግራይ በታቀደው መሰረት የማልማት ስራው ተጀምሯል፡፡ ሂደቱን በቅርበት ከክልሎች ጋር በመሆን ኢንስቲትዩቱ እንዲከታተል በተሠጠው አቅጣጫ መሰረት ክትትልና ድጋፍ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ በዚህ መሠረት የአራቱም ክልሎች የዲዛይን ክለሳ ሥራዎች እና የፓርኩን የግንባታ ሂደት የመከታተልና እና የቴክኒካል ፋስሊቴሽን ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡

### 1.7.6 ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች

**ለሴት ሠራተኞች ምቹ የሥራ አካባቢ ከመፍጠር አንጻር**

በእንስሳት ምርትና መኖ ዘርፍ ውስጥ የተሰማሩ ፈቃደኛ የሆኑ የማምረቻ ድርጅት ባለቤቶች፣ አመራር እና ከኢንዱስትር ሚ/ር፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት ጋር በመተባበር የማምረቻ ድርጅቶቹ ለሴት ሠራተኞች ምቹ የሥራ አካባቢ ከመፍጠር አንፃር ያሉበትን ሁኔታ ለመለየት የሚያስችል መረጃ ከዘርፉ የተለያዩ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ተሰብስቦ በተለዩ ጠናካራና ደካማ ጎኖች ላይ ግብረ-መልስ ተሰጥቷል፡፡ የኢንስቲትዩቱን ሠራተኞች በማወያየት ወላጆቻቸውን በሞት ያጡ ስድስት ሕፃናት በዘለቄታዊነት ቀለባቸውን፣ አልባሳታቸውን እና የትምህርት ቁሳቁስ ወጪያቸውን በመሸፈን ለማስተማር በጠቅላላው 57,886.93 ብር /ሃምሳ ሰባት ሺህ ስምንት መቶ ሰማንያ ስድስት ብር ከዘጠና ሦስት ሳንቲም/ በመሰብሰብ ሠራተኞች ድጋፍ አድርገዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ባለፉት ዓመታት በተቋሙ ሠራተኞች መንግሥት በሚያወጣው ፕሮግራም መሠረት በተለያዩ አካባቢዎች የችግኝ ተከላ ተካሂዷል፡፡

**የሥራ ዕድል ፈጠራን በተመለከተ**

ባለፉት አምስት ዓመታት በንዑስ ዘርፉ ኢንቨስትመንት ለመሳብና ለማሰማራት መንግስት ያለው ጠንካራ ፍላጎትና አቋም ምቹ ሁኔታዎች ቢኖሩም በባለፉት አምስት ተከታታይ ዓመታት በእንስሳት ምርትና መኖ ማቀነባበር ዘርፍ የሚጠበቀውን ያክል የሥራ ዕድል መፍጠር አልተቻለም፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በንዑስ ዘርፉ ማቀነባበሪያዎች በምርት ማምረት ሂደት እና በፕሮጀክት ደረጃ ላይ ባሉ ፕሮጅክቶች 2812 (ወንድ = 1909 ሴት = 903) ቋሚ እና ለ1108 (ሴት = 408 እና ወንድ = 700) ጊዜያዊ በአጠቃላይ በንዑስ ዘርፉ ባለፉት አምስት ዓመታት ለ 3920 ዜጎች ቋሚና ጊዚያዊ የሥራ ዕድል ተፈጥሯል፡፡

በአካባቢ ደህንነት ስራዎች የእንስሳት ምርትና መኖ ማቀነባበሪያዎች የሚለቁትን የሙቀት አማቂ ጋዝ መጠን ለመለካት ያስችል ዘንድ የዘርፉ ፋብሪካዎች የሚጠቀሙት የኃይል ምንጭና መጠን፣ የፍሳሽ ቆሻሻ ማጣሪያ ሁኔታና የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና የአወጋገድ ሥርዓታቸውን እና መሰል አካባቢያዊ ጉዳዮች በየዓመቱ ጥናት እየተደረገ በአለም አቀፍ ደረጃ ሪፖርት ለማድረግ በሚያስችሉ መልኩ መረጃ የማደራጀት ሥራዎች ሲከናወኑ መቆየታቸው በመልካም ጎኑ የተገመገመ ቢሆንም ከልኬት መጠኑ ጋር በተያያዘ ግብረ-መልስ አለመሰጠቱ ክፍተት ያለበት ስለሆነ ለቀጣይ መታረም የሚገባው እንደሆነ ተገምግሟል፡፡

የባዮ-ጋዝ ኢነርጂ ተጠቃሚ ያልሆኑ ሁለት የዘርፉ ማቀነባበሪያዎች የቴክኖሎጂው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሙያዊ ድጋፍ ለማድረግ በታቀደው መሰረት አንድ የወተትና አንድ የሥጋ ማቀነባበሪያ ተጠቃሚ ሆነዋል። የፍሳሽ ማጣሪያ ግንባታን በተመለከተ ሁለት የወተትና ሥጋ ማቀነባበሪያዎች የፍሳሽ ማጣሪያ እንዲያስገነቡ በታቀደው መሰረት ማቀነባበሪያዎቹ የፍሳሽ ማጠራቀሚያ እንዲያስገነቡ ሙያዊ ድጋፍ ተደርጓል።

## 1.8 የውስጣዊና ውጫዊ ሁኔታ ዳሰሳ

### 1.8.1 የውስጣዊ ሁኔታ ዳሰሳ

| ጠንካራ ጎን | ደካማ ጎን |
|---|---|
| • ተልዕኮውን ለማስቀጠል የሚያስችል ተቋማዊ መዋቅር መዘርጋቱ፤<br>• የዝርያ ማሻሻል ሂደት ዘመናዊ እንዲሆን የአባላዘር ማምረቻ ላቦራቶሪ እና ፈሳሽ ናይትሮጂን ማምረቻና ማከፋፈያዎች መኖራቸው፤<br>• በተመረጡ አካባቢዎች የፈሳሽ ናይትሮጂን ማምረቻ ጣቢያዎች ተከፍተው የተሻሻሉ ዝርያዎችን ለአርሶ/ አርብቶ አደሩ እና በዘርፉ ለተሰማሩ ባለሃብቶች ማሰራጨት መቻሉ፤<br>• በተቋሙ የእንስሳት መረጃ ቋት የስራ ክፍል ተደራጅቶ የእንስሳት መረጃዎችን በመሰብሰብ ማደራጀት ላይ መሆኑ፤<br>• ከከፍተኛ ትምህርትና የምርምር ተቋማት ጋር በዘርፉ የቅንጅት ሥራዎች መኖራቸው፤<br>• የእንስሳት የርቢ ፖሊሲ ተዘጋጅቶ መፅደቁ፣<br>• ለአምስት አይነት እንስሳት (የዳልጋ ከብት፣ የወተት ከብት፣ ግመል፣ የዶሮ፣ የአነስተኛ አመንዣጊ እንስሳት) የርቢ እስትራቴጂ ታትሞ መውጣቱ፤<br>• ሶስት የርቢ ፕሮግራሞች (የወተት ከብት፤ የበግ እና ፍየል እንዲሁም የስጋ ከብት) መተግበር መጀመራቸው፤<br>• የአዳቃይ ቴክንሺያኖችን በማሰልጠን ወደ አርብቶ አደሩ ማሰማራት መቻሉ፤<br>• በየማቀነባበሪያዎቹ ክህሎትን ለማሻሻል የስልጠናና ማማከር አገልግሎት መሰጠቱ፤<br>• የወተት ናሙና ምርት ፍተሻ አገልግሎት መሰጠቱ፤<br>• በሥጋ ማቀነባበሪያዎች የምግብ ደህንነት እና ጥራት ማረጋገጫ እንዲያገኙ መደረጉ፤<br>• የአዳቃይ ቴክኒሽያኖች ሥልጠና መሰጠቱ፤ | • የእንስሳት ርቢ ረቂቅ አዋጅ፣ የወተት፣ የማርና ሰም ግብይት ረቂቅ አዋጅ አለመፅደቃቸው፤<br>• የተሰጡ ሥልጠናዎችና ግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች እና የተከናወኑ የቴክኖሎጂ ሽግግር ያመጡትን ተፅዕኖ አለመገምገም፤<br>• ከዶሮ ዝርያ ማሻሻል ጋር ተያይዞ በሃገር ውስጥ ቅድመ መስራች ዘር (grand parental stock) አለመኖር፤<br>• የዝርያ ማሻሻል ቴክኖሎጂዎች ተደራሽነት ውስን መሆን፤<br>• አነሰተኛ አመንዣኪ እንስሳት ላይ የሚሰራው የዝርያ ማሻሻል ስራ ውስን መሆኑ፤<br>• የእንስሳት ውጤቶችን አቀነባብሮ እሴት በመጨመር ለዓለም ገበያ ማቅረብ አለመቻል፤<br>• በዘርፉ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና የግል ባለሃብቱ አጋርነት እና ተሳትፎ ጠንካራ አለመሆን፤<br>• ተቋምማዊ የገጽታ ግንባታ አተገባበር አናሳ መሆን፤<br>• የአባለዘር ማምረቻ ላቦራቶሪዎች በኔትወርክ አለመገናኘት፤<br>• ባለሙያውን የማብቃት ውስንነት መኖሩ፣<br>• የእንስሳት ምርት (ሥጋ፤ወተት ማርና ሰም) ሞዴል ማቀነባበሪያ ሰርቶ ማሳያ አለመኖር፣<br>• በእንስሳት ምርት እሴት ጭማሪና ምርት ልማት ውስንነት መኖሩ፤<br>• የተመራማሪዎች ጥቅማጥቅም በሥራ ላይ ያለመዋል፤<br>• በግብዓት እጥረት ቄራዎች በአቅማቸው ልክ ያለማምረት፤<br>• ከበሽታ ነጻ ቀጠና ያለመኖር፤ |

## 1.8.2 የውጫዊ ሁኔታ ዳሰሳ (መልካም አጋጣሚዎችና ስጋቶች - PESTEL)

| ሁኔታዎች | መልካም አጋጣሚዎች | ሥጋቶች |
|---|---|---|
| ፖለቲካዊ ሁኔታዎች | • የአገሪቱ የውጭ ግንኙነት እየተጠናከረ መምጣቱ፤<br>• መንግሥት ለዘርፉ የሰጠው ትኩረት ከፍተኛ መሆኑ፤<br>• ለእንስሳት ልማት አጋዥ የሆኑ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ፕሮግራሞች መኖራቸው፤ | • በአለም አቀፍ ደረጃ እየተካሄዱ ያሉ ጦርነቶች እና በሀገር ውስጥ የሚከሰቱ ግጭቶች፤<br>• የለጋሽና አበዳሪ አካላት ፖሊሲዎች የራሳቸውን ጥቅም ማዕከል ያደረጉ መሆን፤ |
| ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች | • ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ትስስር እየተፈጠረ መሆኑ፤<br>• ከፍተኛ የእንስሳት ብዛትና አይነት (Genetic diversity) መኖሩ፤<br>• በዘርፉ የተነደፉ እንደሌማት ትሩፋት አይነት ያሉ መርሀ ግብሮች መኖራቸው፣<br>• ለማቀነባበሪያ ግብዓት የሚሆን እምቅ የግብርና አቅም መኖሩ፤<br>• ሀገሪቱ በከፍተኛ ደረጃ እየገነባች ያለችውን ግድቦች መኖራቸው፤<br>• ዘርፉን ለማስፋፋትና ለማልማት ምቹ ሁኔታ መፈጠሩ፤<br>• የኢንቨስትመንት ፍሰት መጨመሩ፤<br>• የኃይል አቅርቦት በተመጣጠነ ዋጋ መቅረቡ፤<br>• የእንስሳት እና እንስሳት ውጤቶች ፍላጎት ከፍተኛ መሆን፤<br>• የኢንቬስትመንት ማበረታቻ ሥርዓት መኖሩ፤<br>• የቴክኒክና የፋይናንስ ዕገዛና ድጋፍ የሚሰጡ የልማት አጋሮች መኖራቸው፤<br>• ዘርፉን የሚያግዙ የተለያዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ፕሮጀክቶች (Food System Resilence Livestock and Fishery Sector Development Program, African Dairy Genetic Gain) እንዲሁም የተለያዩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ፕሮጀክቶች እና የዘርፉ ማህበራት (የሥጋ አምራችና ላኪዎች ማህበር፣ የቁም እንስሳት አድላቢዎች ማህበር፣ ኢትዮጵያ ወተት አምራቾች ማህበር፣ የኢትዮጵያ ወተት አቅራቢዎች ማህበር፣ የኢትዮጵያ ወተት አቀነባባሪዎች ማህበር፣ የኢትዮጵያ መኖ ኢንዱስትሪ ማህበር፣ ኢትዮጵያ ዶሮ አርቢዎችና አቀነባባሪያዎች ማህበር፣ የኢትዮጵያ ንብ ልማት ማህበር ማህበር፣ የኢትዮጵያ አሳ ሀብት እና የውሃ ሳይንስ ማህበር፣ የኢትዮጵያ የእንስሳት ባለሙያዎች ማህበር እና የኢትዮጵያ እንስሳት ሀኪሞች ማህበር) መኖራቸው፤ | • የውጭ ምንዛሪ እጥረት፤<br>• የመሠረተ ልማት አለመሟላት፤<br>• የፋይናንስ አቅርቦት ውስንነት<br>• የመዳረሻ ገበያ ውስንነት<br>• በአለም አቀፍ ደረጃ የተቀባይ ሀገራት ፍላጎት ተለዋወጭ መሆኑ፣<br>• የዓለም ገበያ ዋጋ ተለዋዋጭ መሆን፤ |
| ማህበራዊና አካባቢያዊ ሁኔታዎች | • የሀገሪቱ ሥነምህዳር ለተለያዩ እንስሳት ልማት ምቹ መሆኑ፣<br>• የተደራጁ የዘርፍና የሙያ ማህበራት መኖራቸው፤<br>• በቀላሉ ወደ ሥራ ሊሰማራ የሚችል ከፍተኛ የሰው ሀብት መኖሩ፤<br>• የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መስፋፋት፤<br>• አገሪቱ የምትገኝበት የጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ ለወጪ ንግድ ምርት መዳረሻ አመቺ መሆኑ፤ | • የአየር ንብረት ለውጥ እና እያስከተለ ያለው የተፈጥሮ አደጋ (ለምሳሌ ድርቅ፤ የመኖ እጥረ፤ የእንስሳት ድንበር ተሻጋሪ በሽታዎች መዛመት)፤<br>• የሥራ አጥ ቁጥር መጨመር፤<br>• የሥራ ባህል አለመዳበር<br>• ድርቅ፣ የአየር ንብረት ለውጥ፣ ጎርፍና ሌሎች የተፈጥሮ አደጋዎች ሊከሰት መቻሉ፤ |
| ቴክኖሎጂያዊ ሁኔታዎች | • የኢንፎርሜሽንና ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ እየተስፋፋ መምጣቱ፤<br>• በእንስሳት ምርትና መኖ ኢንዱስትሪ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ እየተስፋፋ መሆኑ፤<br>• ችግር ፈቺ ምርምር እና ስርፀት ሥራዎች ትኩረት መሰጠቱ፤ | • በእንስሳት ምርትና መኖ ቀነባበር ቴክኖሎጂዎችን ለመጠቀም ከፍተኛ ወጪ መጠየቁ፤ |

| ሁኔታዎች | መልካም አጋጣሚዎች | ሥጋቶች |
|---|---|---|
| ህጋዊ ሁኔታዎች | • ለማቀነባበሪያዎች ህጋዊ ከለላ መኖሩ፤<br>• የአሰሪና ሠራተኛ ህግ መኖሩ | • የግብይትና የምርት ጥራት ማስጠበቅ አዋጅ፤ ደንብና መመሪያዎች ላይ የህግ ማዕቀፍና የአፈፃፀም ክፍተት መኖር<br>• ህገ-ወጥ የእንስሳት እና የእንስሳት ውጤቶች ንግድ፤ |

### 1.8.3 አስቻይና ፈታኝ ሁኔታዎች

| አስቻይ ሁኔታዎች (ENABLERS) (ጥንካሬ እና መልካም እድል) | ፈታኝ ሁኔታዎች (CHALLENGES) (ድክመት እና ስጋት) |
|---|---|
| • መንግሥት ለዘርፉ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠቱ የእንስሳት የርቢ ፖሊሲ፣ የአምስት አይነት እንስሳት የርቢ ሰትራቴጂ መፅደቁ እና ሶስት የርቢ ፕሮግራሞች እየተተገበሩ መሆኑ፣<br>• አዳቃይ ቴክንሺያኖችን ማሰልጠን እና የተሻሻሉ ዝርያዎች ለአርሶ/ አርብቶ አደሩ እና በዘርፉ ለተሰማሩ ባለሃብቶች እየተሰራጩ መሆናቸው፤<br>• ከፍተኛ የእንስሳት ብዛትና አይነት (Genetic diversity) መኖሩ በዘርፉ ኢንቨስትመንት ለመሳብ ማስቻሉ፤<br>• በሀገሪቱ ከፍተኛ ሀገር በቀል የእንስሳት ክምችት መኖር እና ለዝርያ ማሻሻል የፈሳሽ ናይትሮጂን ማምረቻ ጣቢያዎች በተመረጡ አካባቢዎች መኖራቸው፣ | • ጥራት ያለው የእንስሳትና እንስሳት ውጤቶች አቅርቦት እጥረት፣ የእንስሳት ምርት ተቀባይ ሀገራት ፍላጎት ተለዋወጭ መሆን እና የአየር ንብረት ለውጥ በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንዳንሆን ማድረጉ፤<br>• የበቃ ባለሙያ እጥረት የእንስሳት ምርትን እሴት ጨምሮ የማምረት ሂደት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ማሳደሩ፤<br>• ከዶሮ ዝርያ ማሻሻል ጋር ተያይዞ በሃገር ውስጥ ቅድመ መስራች ዘር (grand parental stock) አለመኖር በዶሮ ኢንቨስትመንት ላይ ተግዳሮት መፍጠሩ፤<br>• በአነስተኛ አመንዣኪ እንስሳት ዝርያ ላይ እየተሰራ ያለው የዝርያ ማሻሻል ስራ ውስንነት መኖር፤<br>• ያለው የፀጥታ ሁኔታ በእንስሳት ልማት ስራዎች ላይ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚያደርስ መሆኑ፤ |

## 1.8.4 የባለድርሻ አካላት ትንተና

| ተገልጋዮች/ ባለድርሻዎች | ዘርፉከተገልጋዮች/ባለድርሻዎች የሚፈልጋቸው ጉዳዮች | ተገልጋዮች/ባለድርሻዎች ከዘርፉ የሚፈልጉት ምርት/ አገልግሎት | ተገልጋዮች/ባለድርሻዎች በዘርፉ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚያሳድሩባቸው ጉዳዮች | በዘርፉ ላይ የሚያሣድሩት የተፅዕኖ ደረጃ |
|---|---|---|---|---|
| የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት | ▪ ወቅታዊ ግብረ መልስ፤<br>▪ ሁለንተናዊ ድጋፍ፤<br>▪ ወቅታዊና አመቺ ሕጎችን ማውጣት፤<br>▪ የዘርፉ ወገናዊነት፤ | ▪ ህግና ደንብ የተከተለ አሰራር፤<br>▪ ቀልጣፋ፣ ፍትሃዊና ውጤታማ አገልግሎት፤<br>▪ የተስተካከለ ዕቅድና ወቅታዊ ሪፖርት እና የተሟላ መረጃ፤ | ▪ ተገቢ ድጋፍ አለማድረግ፤<br>▪ በጀት መቀነስ፤<br>▪ ለአደረጃጀት ለውጥ መንስኤ መሆን፤ | ከፍተኛ |
| የጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት | ▪ ተገቢውን የአመራር ሚና መወጣት፤<br>▪ ወቅታዊ ግብረ መልስ መስጠት፤<br>▪ አመቺ ፖሊሲ መቅረጽ፤ | ▪ በዕቅዱ የተቀመጡ ዓላማዎችና ግቦች ማሳካት፣<br>▪ ህግና ደንብ የተከተለ አሰራር፣<br>▪ ቀልጣፋ፣ ፍትሃዊና ውጤታማ አገልግሎትና ድጋፍ እና የተሟላ መረጃ፤ | ▪ በዘርፉ የበላይ አመራር ዉሳኔ አሰጣጥ ላይ ጣልቃ መግባት፤<br>▪ ለደመወዝና ጥቅማጥቅም ጥያቄዎች ዉሳኔ አለመስጠት፤ | ከፍተኛ |
| የግብርና ሚኒስቴር | ▪ ለዘርፉ ግብአቶች በጥራት፣ በብዛትና በቀጣይነት እንዲቀርብ ማድረግ፤<br>▪ ቅንጅታዊ አሰራር፤ | ▪ ኢንዱስትሪዎች ከግብርና ጋር ትስስር/ ተመጋባቢነት እንዲኖራቸው፤<br>▪ ቅንጅታዊ አሰራር፤<br>▪ የተሟላ መረጃ፤ | ▪ ለዘርፉ የሚፈለገው ግብአት አለመቅረብ፣<br>▪ የቅንጅታዊ አሰራር ማጓደል፣ | ከፍተኛ |
| ንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒቴር | ▪ የእንስሳትና የእንስሳት ውጤቶች ንግድ ቁጥጥር፣ ወቅታዊ የሥጋና የተረፈ ምርት ዋጋ መከለስ | ▪ የተሟላ መረጃ | ▪ ህገወጥ ንግድ መስፋፋት | ከፍተኛ |
| በዘርፉ የተሰማሩ ባለሀብቶች | ▪ ከሙስና የፀዳ፣ እና በልማታዊ መንገድ ብቻ ማደግ የሚፈልግ<br>▪ ለቀጣይ ልማት የሚተጋ፤<br>▪ መሟላትያለባቸውን መስፈርቶች የሚያሟላ፤<br>▪ የባለቤትነት ስሜት፤<br>▪ እያደገ የሚሄድ ኢንቨስትመንት፤ | ▪ ፍትሐዊ፣ ዘመናዊ፣ ቀልጣፋና ዘመኑን የዋጀ አገልግሎት፤<br>▪ ለሥራቸው አስፈላጊ የሆኑ ሁለንተናዊ ድጋፎች፤<br>▪ ለዘርፉ ኢንቨስትመንት አመቺ የሆነ ከባቢ እንዲፈጠር፤<br>▪ የተሟላ መረጃ፤<br>▪ ሰፊ የገበያ ድርሻ፤ | ▪ በስትራቴጂክ ዕቅዱ የተቀመጡ ዓላማዎችና ግቦች አለመሳካት፤<br>▪ የስራ ግንኙነት መሻከር፤ | ከፍተኛ |
| ገንዘብ ሚኒስቴር | ▪ በቂ በጀት በወቅቱ መመደብ፤<br>▪ በፋይናንስና ግዥ አሰራር የአቅም ግንባታ ሥልጠና፤<br>▪ ለዘርፍ ትኩረት መስጠት፤<br>▪ የፀደቁ የትብብር ስምምነቶች፤ | ▪ ውጤታማ የበጀት አጠቃቀም፤<br>▪ የፋይናንስ ደንብና መመሪያዎች አክብሮ መሥራት፤<br>▪ ወቅታዊ ሪፖርት እና የተሟላ መረጃ፤<br>▪ ተዘጋጅቶ የቀረበ የሥራና የበጀት ዕቅድ፤ | ▪ በቂ ድጋፍ አለማድረግ፤<br>▪ በቂ በጀት አለመመደብና በወቅቱ አለመልቀቅ፤ | ከፍተኛ |
| ኢንቨስትመንት ኮሚሽን | ▪ ልማታዊ ባለሀብት መሳብ፤<br>▪ ለኢንቨስትመንት የተመቻቸ ፈጣን አገልግሎት፤<br>▪ ወቅታዊና የተሟላ የባለሀብት መረጃ፤ | ▪ የተለያዩ የኢንቨስትመንት ፕሮፋይሎች፤<br>▪ ወቅታዊና የተሟላ ለኢንቨስትመንት ውሳኔ የሚረዱ መረጃዎች፤ | ▪ ባለሀብት በሚፈለገው ጥራትና መጠን ያለማግኘት፤ | ከፍተኛ |
| የትምህርት እና የምርምር ተቋማት | ▪ ዘርፉ የሚፈልጋቸውን ባለሙያዎች ማፍራት እና በበቂ ደረጃ ማቅረብ፤<br>▪ በሥርዓተ-ትምህርት ቀረፃና ሥልጠና መሳተፍ፤<br>▪ ችግር ፈቺ የሆኑ የምርምር ውጤቶች፤ | ▪ የዘርፉ የትምህርት ተቋማት ግንኙነት መጠናከር፤<br>▪ አሳታፊነትና የማበረታቻ ሥርዓት መኖር፣<br>▪ የተሟላ መረጃ፤ | ▪ ኢንዱስትሪው የሚፈልጋቸውን ባለሙያዎች በበቂ ደረጃ አለማግኘት፤<br>▪ ችግር ፈቺ የሆኑ የምርምር ውጤቶችን አለማግኘት፤ | ከፍተኛ |

| ተገልጋዮች/ ባለድርሻዎች | ዘርፉከተገልጋዮች/ባለድርሻዎች የሚፈልጋቸው ጉዳዮች | ተገልጋዮች/ባለድርሻዎች ከዘርፉ የሚፈልጉት ምርት/ አገልግሎት | ተገልጋዮች/ባለድርሻዎች በዘርፉ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚያሳድሩባቸው ጉዳዮች | በዘርፉ ላይ የሚያሣድሩት የተፅዕኖ ደረጃ |
|---|---|---|---|---|
| ገቢዎች ሚ/ር እና ጉምሩክ ኮሚሽን | ▪ ቀልጣፋ፣ ፍትሃዊና ውጤታማ አገልግሎት መስጠት፤<br>▪ ቅንጅታዊ አሰራርና ወቅታዊ መረጃ፤<br>▪ ለዘርፍ ቅድሚያ መስጠት፤ | ▪ ማበረታቻ የተፈቀደላቸው ድርጅቶች፤ ዝርዝር መረጃ፤<br>▪ ቅንጅታዊ አሰራር፤ | ▪ በድርጅቶች የአለም ገበያ ተወዳዳሪነት ላይ ተፅእኖ መፍጠር፤<br>▪ ለኢንቨስትመንት የሚሰጡ ማበረታቻዎች ተፈጻሚ እንዳይሆኑ ተፅዕኖ መፍጠር፤ | ከፍተኛ |
| ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን | ▪ የሰው ሀብት አቅም መገንባት፤<br>▪ ባለሙያን ሊያቆይና ሊስብ የሚችል የደመወዝ ስኬልና ጥቅማ ጥቅሞች፤<br>▪ የልዩ ድጋፍ እርምጃ (affirmative action) ተግባራዊነት፤ | ▪ ሜሪትን መሠረት ያደረገ የሠራተኞች ቅጥር/ ዕድገት፤<br>▪ ህግና ደንብ አክብሮ መሥራት፤<br>▪ የተሟላና ወቅታዊ መረጃ፤<br>▪ የለውጥ ፕሮግራሞች ተግባራዊነት፤<br>▪ የልዩ ድጋፍ እርምጃ ተግባራዊ ማድረግ፤ | ▪ አመኔታ ማጣት፤<br>▪ ድጋፍ መንፈግ፤ | ከፍተኛ |
| የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር | ▪ ኢንቨስትመንትን መሳብ፤<br>▪ ለማኑፋቸቱሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ቅድሚያ መስጠት፤<br>▪ የተሟላ መረጃ፤<br>▪ ገበያን ማፈላለግና ማስተሳሰር፤ | ▪ ወቅታዊና የተሟላ መረጃ፣<br>▪ ቅንጅታዊ አሰራር፣ | ▪ የኢንቨስትመንትና ገበያ መስፋፋት በሚፈለገው ደረጃ አለመሆን፣ | ከፍተኛ |
| የክልል መንግስታት እና የከተማ አስተዳደሮች | ▪ ቀልጣፋ የሆነ የመሬትና የመሠረተ ልማት አቅርቦት፤<br>▪ ባለሀብቶች በአካባቢያቸው ለሚያጋጥሟቸው ችግሮች ፈጣን ምላሽ መስጠት፤<br>▪ ወቅታዊና የተሟላ መረጃ፤<br>▪ ቅንጅታዊ አሰራር መፍጠር፤<br>▪ ግብአት አቅርቦት፤ | ▪ ወቅታዊና የተሟላ መረጃ፤<br>▪ ልማታዊ ባለሀብቶች ሚዛናዊ በሆነ መልክ በየክልሉ ኢንቨስት እንዲያደርጉ፤<br>▪ የቅንጅት ስራዎች እና የተለያዩ ድጋፎች፤<br>▪ ቅንጅታዊ አሰራርና ወቅታዊ መረጃ፣<br>▪ የተዘጋጁና የተገነቡ ኢንዱስትሪ ዞኖች፣ | ▪ የኢንቨስትመነት ስራን ማጓተት፤<br>▪ አመኔታ ማጣት፤<br>▪ ቅንጅታዊ አሰራር ማጓደል፤ | ከፍተኛ |
| የመሠረተ ልማት ተቋማት(ኤልፖ፣ ቴሌ፣ መንገድ፣ውኃ) | ▪ ቀልጣፋና ተወዳዳሪ የመሠረተ ልማት አቅርቦት፤<br>▪ የተሟላ መረጃ፤ | | ▪ የሚፈለገውን የመሠረተ ልማት አቅርቦት አለማቅረብ፣ | ከፍተኛ |
| የፋይናንስና መድህን ተቋማት | ▪ ትኩረት ለተሰጣቸው ዘርፎች በቂ የፋይናንስ አቅርቦት፤<br>▪ ቅንጅታዊ አሠራር፤<br>▪ የተሟላ መረጃ፤<br>▪ ምቹ የፋይናንስ ፖሊሲ፤ | ▪ ቅንጅታዊ አሠራር፣<br>▪ የተሟላ መረጃ፤ | ▪ የሚሰጠውን ብድር ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ዘርፎች በወቅቱ አለመልቀቅ፤ | ከፍተኛ |
| መገናኛ ብዙኃን | ▪ የዘርፉ ምርቶች በሀገር ውስጥና በውጭ ገበያ እንዲተዋወቅላቸው፤<br>▪ ባለድርሻ አካላት በዘርፉ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ የሚረዳ የተሟላና ወቅታዊ መረጃ እንዲያቀርቡ፤ | ▪ ባለሀብቶችን ወደዘርፉ ለመሣብ የሚያግዙ መረጃዎች፤<br>▪ ቅንጅታዊ አሠራር፤ | ▪ በቂ የሚዲያ ሽፋን አለመስጠት፤ | መካከለኛ |

| ተገልጋዮች/ ባለድርሻዎች | ዘርፉከተገልጋዮች/ባለድርሻዎች የሚፈልጋቸው ጉዳዮች | ተገልጋዮች/ባለድርሻዎች ከዘርፉ የሚፈልጉት ምርት/ አገልግሎት | ተገልጋዮች/ባለድርሻዎች በዘርፉ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚያሳድሩባቸው ጉዳዮች | በዘርፉ ላይ የሚያሣድሩት የተፅዕኖ ደረጃ |
|---|---|---|---|---|
| መንግታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች | ▪ ለስትራቴጂክ ዕቅዱ መሳካት የድርሻቸውን እንዲወጡ፤<br>▪ የሚሰጡት ድጋፎች በወቅቱና በተገቢው መልክ ተግባራዊ የተደረጉ መሆናቸው፤<br>▪ ለዘርፉ ዕድገት የበኩላቸውን አስተዋፅኦ የሚያበረክቱ፤ | ▪ በዘርፉ የተጠኑ አዋጭነት ያላቸው የፕሮጀክቶች ጥናት ሠነድ፤<br>▪ ልዩ ልዩ ማበረታቻዎችና ድጋፎች፤<br>▪ ግልጽ፣ ቀልጣፋና ፈጣን አገልግሎት፤ | ▪ የዘርፉ ዕቅድ ስኬታማ አለመሆን፤ | መካከለኛ |
| ባዮ ዳይቨርሲቲ | ▪ የሀገሪቱን ብዝሃ-ሀይወት መጠበቅ<br>▪ የዝርያን ትክክለኛነት ማረጋገጥ<br>▪ ስለሀገሪቱ ዝርያ ጥብቅና መቆም | • በምርምር የተገኙ ዝርያዎችን ስነ-ምህዳር ተስማሚነት መፈተሽ | የዝርያ መመናመንና መጥፋት | ከፍተኛ |
| የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት | ▪ የእንስሳትን ጤና ማረጋገጥ | መረጃና ግብረ መልስ | ጥራቱን የጠበቀ የክትባትና መድሃኒት አለማቅረብ | ከፍተኛ |
| አርሶ/አረብቶ አደር | ▪ በተመረጡ ዝርያዎች እንስሳቶቻቸውን ያረባሉ<br>▪ ምርጥ ዝርያ ያላቸውን እንስሳት ያባዛሉ<br>▪ ሀገር በቀል እውቀታቸውን እና ልምዳቸውን ያካፍላሉ<br>▪ በዘርፉ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን የጠቀማሉ | ▪ የተሻሻለ የእንስሳት ዝርያ<br>▪ የቴክኖሎጂ ግብኣት<br>▪ የምክር አገልግሎት እና የምርምር ውጤት | ▪ የምርምር ውጤቶችን ባለመቀበል<br>▪ በአሰራር ሂደት ባለመሳተፍ | ከፍተኛ |
| የዘርፍ/የሙያ ማህበራት | ▪ በልማቱ ላይ የነቃ ተሳትፎ በማድረግ በዘመናዊ የዝርያ ቴክኖሎጂ መስፋፋት የድርሻቸውን እንዲወጡ፤<br>▪ ችግር ፈቺ የሆኑ የምርምር ውጤቶች፣ለአባላቶቻቸው ያጋራሉ ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ<br>▪ የዘርፉ አላማ እንዲሳካ የማመቻቸት ሰራ ይተገብራሉ | ▪ አሳታፊ የሆነ የአሠራር ሥርዓት፣<br>▪ አመቺ የሆነ የሥራ አካባቢ፣<br>▪ የሙያ እገዛ እና ምክር<br>▪ አዳዲስ የቴክኖሎጂ ግብዓት<br>▪ የምርምር ውጤቶች<br>▪ አስተዳደራዊ ድጋፍ<br>▪ አሳታፊ የሆነ የአሠራር ሥርዓት፤<br>▪ ወቅታዊ መረጃ፤ | ▪ ማበርከት የሚገባቸውን አስተዋፅኦ መንፈግ፤<br>▪ ለቅንጅት ሥራዎች ተባባሪ አለመሆን | መካከለኛ |

## 1.9. ተልዕኮ፣ ራዕይ፤ ዓላማና ዕሴቶች

### 1.9.1 ዓላማ

የኢንስቲትዩቱ ዓላማ የሀገራችንን እንስሳት ሀብት ዝርያ ምርታማነት፣ ምርት ልማት፣ ጥራትና የገበያ ተወዳዳሪነትን በማሳደግ አካባቢያዊ ዘላቂነትንና ተደራሽነትን ባረጋገጠ መልኩ ዘርፉ ለኢኮኖሚ ዕድገትና ለሀገር ብልጽግና የላቀ አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ማድረግ ነው።

### 1.9.2 ተልዕኮ

የእንስሳት ዝርያን በማሻሻል ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ፣ በዘርፉ ጥናትና ምርምር በማካሄድ፣ በአቅም ግንባታና ማማከር፣ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በማልማትና በማሸጋገር፣ ኢንቨስትመንትና ገበያ እንዲስፋፋና እንዲቀላጠፍ ድጋፍ በማድረገ ደረጃቸውን የጠበቁና ተወዳዳሪ የሆኑ ምርቶችን ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ በብዛት፣ በጥራትና ደህንነቱ ተጠብቆ እንዲቀርብ በማድረግ የሕብረተሰቡን ተጠቃሚነት ማረጋገጥና ሀገሪቱ ከዘርፉ የምታገኘውን ገቢ ማሳደግ ነው።

### 1.9.3 ራዕይ

በ2022 ኢንስቲትዩቱ በእንስሳት ዝርያ ማሻሻል እና በእንስሳትና እንስሳት ተዋጽኦ ምርቶች ማቀነባበር የምርምር፣ የሥልጠና፣ የማማከር እና የቴክኖሎጂ ሽግግር በአፍሪካ ቀዳሚ የብቃት ማዕከል ሆኖ ማየት፣

### 1.9.4 እሴቶች

- ቅንነት
- ለለውጥ ዝግጁነት
- አገልጋይነት
- አርአያነት
- የቡድን ሥራ
- ግልጸኝነት
- ተጠያቂነት
- ከሙስና የፀዳ አሰራር
- አሳታፊነት

# ክፍል ሁለት፡- እስትራቴጂያዊ ዓላማዎች፤ ግቦች፣ ዒላማዎች እና የማስፈፀሚያ ስልቶች

## 2.1 እስትራቴጂያዊ ዓላማዎች

ኢንስቲትዩቱ የእንስሳት ሀብት ዝርያ ምርታማነትን ማሻሻል፤ የእንስሳት ምርትና መኖ ማቀነባበሪያዎች ሁለገብ ተወዳዳሪነትን በማረጋገጥ፣ የምርት ጥራት፣ደህንነትና የገበያ ተደራሽነት እና ተወዳዳሪነትን በማሳደግ አካባቢያዊ ዘላቂነትንና ተደራሽነትን ባረጋገጠ መልኩ ለኢኮኖሚ ዕድገት የላቀ አስተዋፆ የሚያደርጉ ስትራቴጂያዊ ዓላማዎች ተለይተዋል።

**የእቅድ ዘመኑ እስትራቴጂያዊ አላማዎች፡-**

- እስትራቴጂክ ዓላማ አንድ፡- የእንስሳት ዝርያ በማሻሻል ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ፤
- እስትራቴጂክ ዓላማ ሁለት፡- የእንስሳት ምርትና መኖ ማቀነባበሪያዎችን ተወዳዳሪነት ማሳደግ፤

## 2.2 እስትራቴጂያዊ ግቦች

እስትራቴጂያዊ አላማዎችን ለማሳካት በእቅድ ዘመኑ አስፈላጊ ስራዎችን በማከናወን ሊደረስባቸው የሚገቡ የሚከተሉት ስትራቴጅያዊ ግቦች ተቀርጸዋል።

ግብ 1፡-የእንስሳት ዝርያ ማሻሻል

ግብ 2፡-የግብዓት አቅርቦትና ስርጭትን ማሳደግ

ግብ 3፡- የተቀነባበረ የእንስሳት ምርትና መኖ፣ ጥራት፣ ደህንነት እና ምርታማትን ማሳደግ

ግብ 4፡- የጥናት፣ ምርምርና ስርፀት ማሳደግ

ግብ 5፡-ኢንቨስትመንትና ገበያ ማስፋፋት

ግብ 6፡- የዝርያ ማሻሻል፣ የተቀነባበረ የእንስሳት ምርት እና መኖ መረጃ አጠቃቀም ማሳደግ፣

ግብ 7፡-ቴክኖሎጂ ማሸጋገር፣ማላመድ እና ማስረፅ፣

ግብ 8፡- የዘርፉን የሰው ሀይል አቅም መገንባት፣

ግብ 9፡- ዘርፈ ብዙ ጉዳዮችን ማሻሻል፣

## 2.3. የግብ ዒላማዎች በዋና ዋና አመልካቾች

የታለሙትን ስትራቴጂክ አላማዎች ስኬት ለማረጋገጥ በእቅድ ዘመኑ ሊደረስባቸው የሚገቡ የግብ ኢላማዎች (Targets) በዋና ዋና አመልካቾች ታቅደዋል።

### ግብ 1፡- የእንስሳት ዝርያን ማሻሻል

- ➢ ሶስት ነባር የዳልጋ ከብት የዝርያ ማሻሻል የብዜት ማዕከላት (ዲዳ ጢያራ፣ ወላይታ ሶዶ፣ ቻግኒ እና ሁመራ) ማጠናከርና ተጨማሪ ሶስት ማዕከላት በመንግስትና በግል ባለሃብቶች ማቋቋም፣
- ➢ አዳዲስ ማህበረሰብ አቀፍ የሥጋና ወተት ዝርያን ለማሻሻል በበግና ፍየል እርባታ ፕሮግራሞች በእቅድ ዘመኑ 30 ማህበራት ማቋቋም፣

- የአውራ ፍየል አቅርቦትና ሥርጭት በመነሻ ከነበረት 953 በየዓመቱ ቁጥሩን በ10 በመቶ በማሻሻል በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 2572 ማድረስ፣
- የአውራ በግ አቅርቦትና ሥርጭት ከነበረው 3811 አውራ በጎች በየዓመቱ ቁጥሩን በ10 በመቶ በማሻሻል በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 10289 ማድረስ፣
- የተሻሻሉ የወተት ላሞች የተጠቀሙ አርሶ/አርብቶ አደሮች ቁጥር በ2012 ከነበረበት 28% በ2022 ዓ.ም ወደ 59% ማሳደግ፣
- አርሶ/ አርብቶ አደሩን በተለያዩ የእንስሳት እርባታ እና ዝርያ ማሻሻል ሥራዎች ተጠቃሚ እንዲሆን በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ ወደ 1.3 ሚሊዮን አርሶ አደሮች ማሳተፍ፣
- በማህረሰብ አቀፍ የበግና ፍየል እርባታ ፕሮግራም የአርሶ/አርብቶ አደሩን ተሳትፎ በ2012 መጨረሻ ከነበረበት 20 በመቶ በየዓመቱ በ10 በመቶ እያደገ በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 51.8 በመቶ ማድረስ፣
- የተሻሻሉ የወተት ዲቃላ ላሞች የቀን የወተት ምርት አሁን ከደረሰበት 6 ሊትር በአማካይ 4% በማሳደግ በ2022 መጨረሻ 10.74 ሊትር ማድረስ፣
- በጊደር ማራቢያ ማዕከላት የሚወለዱ ጥጆች ቁጥር በዕቅዱ ዘመን መጨረሻ ወደ 400 ማሳደግ፣
- በተሻሻሉ ኮርማዎች፣ በሲንክሮናይዜሽን፣ ፆታው በተለየ አባላዘር በማዳቀል እና በመደበኛ ድቀላ በማህበረሰቡ የሚወለዱ የጥጆች ቁጥር በዕቅዱ ዘመን መጀመሪያ ከደረሰበት 51030 በየዓመቱ 10 በመቶ እያደገ በ2022 መጨረሻ ወደ 1,364,102 ማሳደግ፣
- የሰው ሰራሽ የማዳቀል ዘዴ በቀላሉ ማዳረስ በማይቻልባቸው በታዎች 54 የኮርማ አገልግሎት ጣቢያዎችን ማቋቋም፣
- የመስክ ማዳቀል አገልግሎት ውጤታማነትን /Field AI Efficiency/ ለማሻሻል በዕቅዱ ዘመን መጀመሪያ ከደረሰበት 2.27 በአማካይ በዓመት በአማካይ 3.56% በመቀነስ የጥቂ ድግግሞሹን በ2022 መጨረሻ 1.91 ማድረስ፣
- የአሳ ብዜት ማዕከላትን ከሁለት ወደ 15 በማሳደግና 63 ሚሊዮን የዓሳ ጫጩት በውሃ አካላት ላይ በመጨመር የአሳ ዝርያን ማሻሻል፣
- በእቅዱ መጨረሻ አንድ የቅድመ መስራች ዘር (Grand parent stock) እንዲቋቋም ማድረግ፣
- አንድ የንግሥት ንብ ብዜትና ማሰልጠኛ ማዕከል በማቋቋም አሁን ካሉት አምስት ማዕከላት በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ ወደ ስድስት ማሳደግ፣
- የተሻሻለ የንብ ዝርያ ስርጭት አሁን ካለበት 68 እናት ንብ ተደራሽነት በ2022 በጀት ዓመት መጨረሻ ወደ 680 እናት ንብ ማሳደግ፣.
- የተሻሻሉ የንብ መኖ ችግኝ ሥርጭት አሁን ካለበት 46,000 በ2022 በጀት ዓመት መጨረሻ ወደ 150,000 ማሳደግ፣

## ግብ 2፦ የግብዓት አቅርቦትና ስርጭት ማሳደግ

- ለአባለዘር ምርት የሚውሉ ዝርያቸው የተሻሻሉ ኮርማዎች ከ 47 በአማካይ በየዓመቱ በ38 በመቶ በማሳደግ በ2022 ዓ.ም መጨረሻ 189 ማድረስ፣
- የአባለዘር ምርት በዕቅዱ ዘመን መጀመሪያ ከደረሰበት 1,474,230 ዶዝ በአማካይ በየዓመቱ በ38.3 በመቶ እያደገ በ2022 መጨረሻ ወደ 7,465,832 ዶዝ ማሳደግ፣
- በኢንስቲትዩትና በክልሎች አሁን ያሉትን 22 የፈሳሽ ናይትሮጂን ማምረቻ ማሽኖች ወደ 30 በማሳደግ የፈሳሽ ናይትሮጂንን ዓመታዊ ምርትን በዕቅዱ ዘመን መጀመሪያ ከነበረበት 287,000 ሊትር በአማካይ

በየዓመቱ በ13.8 በመቶ በማሳደግ በ2022 ዓ.ም መጨረሻ 650,000 ሊትር ማድረስ፣

- ፆታው የተለየ አባላዘር (sexed semen) በዕቅዱ ዘመን መጀመሪያ ከደረሰበት 15,000 ዶዝ በአማካይ በየዓመቱ 20 በመቶ እያደገ በ2022 መጨረሻ ወደ 92,878 ዶዝ ማድረስ፣
- ለድራት ሆርሞን አገልግሎት የሚውል ሆርሞን በዕቅዱ ዘመን መጀመሪያ ከደረሰበት 16,000 በአማካይ በየዓመቱ 20 በመቶ በማሳደግ በ2022 መጨረሻ ወደ 100,000 ማድረስ፣
- የዶሮ ዝርያዎች አቅርቦትና ሥርጭት ለማሻሻል የመስራች ዘር (parent stock) በ2022 መጨረሻ ወደ 340,00 ቁጥር ማድረስ፣
- አንድ መቶ አርብቶ አደሮችን ከቄራዎች ጋር በኮንትራት እርባታ ማስተሳሰር

## ግብ 3፡- የተቀነባበረ የእንስሳትና ምርትና መኖ፣ ጥራት፣ ደህንነት እና ምርታማትን ማሳደግ

- የእንስሳት ምርትና መኖ ማቀነባበር ኤክስፖርት የውጭ ምንዛሪ ግኝት በ2012 በጀት ዓመት ተገኝቶ የነበረውን 72.48 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር በ2022 በጀት ዓመት መጨረሻ ወደ 1.19 ቢሊዮን ማሳደግ፣
- ተቀነባብሮ ለዉጪ ገበያ የቀረበ የበግና ፍየል ሥጋ ምርት አሁን ካለበት 11,438.30 ቶን በ2022 ዓ.ም 158,659 ቶን በማድረስ 973.70 ሚሊዬን ዶላር ገቢ ማስገኘት፣
- የዳልጋ ከብት ሥጋ ምርት አሁን ካለበት 380.75 ቶን በ2022 ዓ.ም 1,570.54 ቶን በማድረስ 5.67 ሚሊዬን ዶላር ገቢ ማስገኘት፣
- የእርድ ተረፈ ምርት አሁን ካለበት 2461.9 ቶን በ2022 ዓ.ም 52,855.27 በማድረስ 123.73 ሚሊዬን ዶላር ገቢ ማስገኘት፣
- የማር ምርት አሁን ካለበት 150.09 ቶን በ2022 ዓ.ም 791.60 ቶን በማድረስ 4.77 ሚሊዬን ዶላር መስገኘት፣
- የሰም ምርት አሁን ካለበት 235.01 ቶን በ2022 ዓ.ም 1,666.72 ቶን በማድረስ 15.29 ሚሊዬን ዶላር ማስገኘት፣
- የዓሳ ምርት አሁን ካለበት 373.56 ቶን በ2022 ዓ.ም 4841.48 ቶን በማድረስ 1.66 ሚሊዮም ዶላር ገቢ ማስገኘት፣
- የዶሮ ምርት ኤክስፖርት በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 1465.80 ቶን በመላክ 5.02 ሚሊዮም ዶላር ገቢ ማስገኘት፣
- የተቀነባበረ የመኖ ምርት ኤክስፖርት በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 90,190.02 ቶን በመላክ 64.76 ሚሊዮም ዶላር ገቢ ማስገኘት፣
- የወተት ተዋጽኦ ምርት አሁን ካለበት 0.77 ሚሊዬን ሊትር በ2022 ዓ.ም 38.07 ሚሊዬን ሊትር በማድረስ 3.30 ሚሊዬን ዶላር ገቢ ማስገኘት፣
- ተቀነባብሮ ለሀገር ውስጥ ገበያ የሚቀረብ ወተት ምርት መጠን አሁን ካለበት 105.7 ሚሊዬን ሊትር በ2022 ዓ.ም 192.36 ሚሊዬን ሊትር ማድረስ፣
- የቀነባበረ የመኖ ምርት መጠን ዕድገት አሁን ካለበት 135,32 ቶን በ2022 ዓ.ም ወደ 2991.42 ቶን ማሳደግ፣
- የዶሮ ሥጋ ምርት መጠን ዕድገት አሁን ካለበት 1752 ቶን በ2022 ዓ.ም ወደ 12615.64 ቶን ማሳደግ፣
- ከውጭ የሚገቡትን የዘርፉ ምርቶች በሀገር ውስጥ ምርት እንዲተካ ድጋፍ በማድረግ ምርቶቹን ለማስገባት የሚወጣውን ስድስት (6 ሚሊየን ዶላር) ማስቀረት
- በ ዕቅድ ዘመኑ 34 የእንስሳት ምርትና መኖ ማቀነባበሪያዎች የቤተ-ሙከራ እውቅና (Accreditation) እንዲያገኙ ማድረግ፣

- የእንስሳት ምርት ማቀነባበሪያዎች የምግብ ደህንነት አስተዳደር ስርዓት፣ ሰርቪላንስ ኦዲት፣ መልካም አመራረት ሂደት፣መልካም የንፅህና ሂደት የተገበሩ ፋብሪካዎች ከ 12 ወደ 32 ማሳደግ፣
- በኢንስቲትዩቱ አንድ የእንስሳት ምርት እና መኖ ማቀነባበሪያ ጥራት ፍተሻ ላቡራቶሪ መገንባት፣
- የእንስሳት ምርትና መኖ ጥራት ናሙና ፍተሸና ትንተና አሁን ካለው 150 ወደ 300 ማሳደግ፣
- በኢንስቲትት አምስት ዘመናዊ (ሞዴል) የእንስሳት እርባታና ማቀነበበሪያ መገንባት እና አለም አቀፍ ምርጥ ተሞክሮ ካላቸው ሁለት ሀገራት ጋር ቁርኝት መፍጠር፣
- በመኖ ሰርቶ ማሳያ 95 ቶን የተሻሻሉ የመኖ እፅዋት ማልማት፣

## ግብ 4 የጥናት፣ ምርምርና ስርፀት ማሳደግ

- በዕቅዱ ዘመን 10 የምርምር እና 20 የተለያዩ የጥናት ስራዎችን ማከናወንና ማሳተም፣
- በዕቅድ ዘመኑ በዝርያ ማሻሻልና ምርትና መኖ ማቀነባበር በተሰራጩ ቴክኖሎጂዎች አስራ ሁለት የተጽዕኖ ግምገማ ማካሄድ፣
- የንዑስ ዘርፉ አምራቾች/አቀነባባሪዎች ከአካባቢዉ ማህበረሰብ ጋር ያላቸዉን መስተጋብር አስራ ሁለት ግምገማዎችን ማካሄድ፣
- በእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ፣ እንስሳት ምርትና መኖ ማቀነባበር ላይ የተሰጡ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች ያመጡትን ተፅዕኖ ስድስት ግምገማዎች ማካሄድ፣
- የዘርፉን ምርታማነት ለማሳደግ የምርት አዋጭነት /Economical production/ በአምስት የምርት አይነቶች ማካሄድ፣
- በዘርፉ ኢንቨስትመንት ላይ ለመሰማራት ተዘጋጅተዉ የሚቀርቡ አስራ ስምንት የቢዝነስ ፕሮፖዛሎችን በመገምገም ለተጠቃሚዎች ግብረ መልስ መስጠት፣

## ግብ 5፡- ኢንቨስትመንትና ገበያ ማስፋፋት

- በእንስሳት ዘርፍ አዳዲስ ኢንቨስትመንቶችን አሁን ከደረስንበት ከ 7 በ2022 በጀት አመት መጨረሻ ወደ 50 ማድረስ፣
- የተጀመሩ ኢንቨስትመንቶችን እንዲጠናቀቁ በማድረግ በእቅድ ዘመኑ 43 ኢንቨስትመንቶችን ወደ ስራ ማስገባት፣
- የኤክስፖርት መዳረሻ ገበያዎች በማስፋት አሁን ካለባት 4 የመደራሻ ሀገራት በ2022 ወደ 9 (ቻይና፣ ቬትናም፣ ማለዚያ፣ እንዶነዥያ እና ሞሪሽየስ) ማድረስ፣
- ሶስት የርቢ፣ የወተት፣ የማርና ሰም የግብይት አዋጆች ማፀደቅ፣
- በኤክስፖርት ቄራዎች እየተከሰተ ያለውን የእንስሳት አቅርቦት እጥረት ለመፍታት ስድስት የእንስሳት እርባታ (ራንች) በግል ባለሀብቱ እንዲቋቋም የቴክኒክ ድጋፍ መስጠትና በተመሳሳይ ሁኔታ አንድ የግብይት መመሪያ ማዘጋጀት፣

## ግብ 6፡- የእንስሳት ዝርያ ማሻሻል፣ ምርት እና ተዋፅኦ ማቀነባበር መረጃ ማሳደግ

- በእቅድ ዘመኑ አንድ የአነስተኛ አመንዣኪ እንስሳት መረጃ ቋት መመስረት፣
- የተመዘገበ አነስተኛ አመንዣኪ እንስሳት ምርታማነት መረጃ ቁጥር በዕቅዱ መጨረሻ 188,000 ማድረስ፣
- አዲስ የተመዘገበ የወተት ከብት እርባታ ቁጥር አሁን ካለበት 4106 በ2022 ዓ.ም መጨረሻ 5000 ማድረስ፣
- የተመዘገበ የወተት ከብት ምርታማነት መረጃ ቁጥር አሁን ካለበት 83311 በ 2022 መጨረሻ ወደ 180,000

ማድረስ፣

- የወተት ንጥረ ነገር ይዘት ናሙና ዓመታዊ የምርመራ አቅም በማሳደግ በዕቅዱ ዘመን መጨረሻ 7000 ማድረስ፣
- የሶማቲክ ሴል (SCC) ናሙናዎች ዓመታዊ የምርመራ አቅም በማሳደግ በዕቅዱ ዘመን መጨረሻ 7000 ማድረስ፣
- የእንስሳት ዘረመል ምርመራ በእቅድ ዘመኑ በአጠቃላይ 11100 ምርመራ ማካሄድ፣
- በእቅድ ዘመኑ በየዓመቱ አራት ጊዜ የእንስሳት ዝርያ መረጃ ትንተና (EBV) ማካሄድ እና በየሳምንቱ ግብረ መልስ መስጠት
- አንድ የእርድ እንስሳት ግብይት እሴት ሰንሰለት ዲጂታል የገበያ መረጃ ስርዓት መዘርጋት

## ግብ 7፡- ቴክኖሎጂ ማሸጋገር፣ ማላመድ እና ማስረፅ

- በዕቅዱ ዘመን መጨረሻ የእንስሳት ዝርያ ለማሻሻል የሚያስችሉ ስድስት ቴክኖሎጆዎችን ማላመድና ማስረፅ፣
- የእንስሳት ምርት ማቀነባበር ምርታማናትን ለማሻሻል የሚያስችሉ ስድስት ቴክኖሎጆዎችን ማላመድና ማስረፅ፣

## ግብ 8፡- የዘርፉን የሰው ሀይል አቅም መገንባት

- በዓመት 31 የነበረውን የአዳቃይ ቴክኒሺያኖች የማሰልጠን አቅም ወደ 600 ማሳደግ፣
- የተሃድሶ ስልጠና የሚሰጣቸው የአዳቃይ ተክኒሽያንኖች 50 ማድረስ፣
- የፈሳሽ ናይትሮጂን ኦፕሬተሮች ከ 20 ወደ 35 ማሳደግ፣
- በየአመቱ ለ15 የአባላዘር ላብራቶሪ ቴክኒሽያን ስልጠና መስጠት፣
- ለ800 የወተት ከብት አርቢዎች ስልጠናን መስጠት፣
- ለመረጃ መዝጋቢ ባለሙያዎች የሚሰጠውን ስልጠና ከ 20 ወደ 160 ማሳደግ፣
- በየዓመቱ በአማካይ 819 የእንስሳት ምርትና መኖ ማቀነባበርሪያ ባለሙያዎች ማሰልጠን

## ግብ 9፡- ዘርፈ-ብዙ ጉዳዮችን ማሻሻል

- የሙቀት ጋዝ ቅናሳ በ2012 ከተደረሰበት 12.06 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን በ2022 48 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን ማድረስ፣
- በኢንስቲትዩቱ ውስጥ አንድ እና በእንስሳት እርባታና ምርት ማቀነባበሪያዎች 30 የባዮ ጋዝ ፕላንት ማቋቋም፣
- በእንስሳት ምርት ማቀነባበሪያዎች የፈሳሽ ቆሻሻ ማጠሪያ ፕላንት አሁን ካለው 2 በእቅዱ መጨረሻ ወደ 12 ማሳደግ
- የአከባቢ ጥበቃ አስተዳዳር ስርዓት(ISO 14001:2015 ) በ 14 ሥጋ እና ተረፈ ምርት ማቀነባበሪያዎች ተግባራዊ ማድረግ፣
- በእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ማዕከላት እና በእንስሳት ምርት ማቀነባበሪያዎች የአከባቢ ተፅዕኖ ቅነሳ በ48 ድርጅቶች ተግባራዊ ማድረግ፣
- በእንስሳት ልማት ዘርፍ የሥራ ዕድል ፈጠራ አሁን ካለው 2812 ቋሚ እና 1108 ጊዚያዊ በ2022 ወደ 7053 ቋሚና እና 14957 ጊዚያዊ ማሳደግ

## 2.4 ዋና ዋና የስትራቴጂክ እቅዱ ማስፈጸሚያ ስልቶች

### 2.4.1 ቅንጅታዊ ስራዎችን ማጠናከር

የእንስሳት እሴት ሰንሰለት በርካታ ተዋንያን ያሉበት ሲሆን የእንስሳት ልማቱን ውጤታማ በማድረግ ዘርፉ ለሀገር ኢኮኖሚ የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ ለማሳደግ ከእነዚህ ተዋንያን ጋር በቅንጅትና በትብብር መስራት አስፈላጊ ነው፡፡ ለአብነትም ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት፣ የክልልና የፌደራል ምርምር ተቋማት፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶች፣ ማህበራት፣ በዝርያ ማሻሻል፣ ምርት ማቀነባበርና ገበያ ልማት ላይ የተሠማሩ የግል ባለሀብቶችና ከተለያዩ መንግስታዊ ተቋማት ጋር በርካታ ስራዎች በቅንጅት ሲሰሩ የነበሩና አሁንም በመሰራት ላይ ናቸው፡፡ በቀጣይ አመታትም በስትራቴጂክ እቅዱ የተወጠኑ ግቦችንና የተጣሉ ኢላማዎችን ለማሳካት ለቅንጅት ስራዎች ትኩረት በመስጠትና በእቅድ አካቶ የማከናወን ስልት ተግባራዊ ይሆናል፡፡

### 2.4.2 የግል ባለሀብቱን ሚና እና ተሳትፎ ማረጋገጥ

በአሥር ዓመቱ በሀገራዊ ስትራቴጂክ የልማት እቅዱና ሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ ዕቅዱ ላይ እንደተመለከተው የግል ባለሀብቱ በልማትና እድገት ውስጥ የማይተካ ሚና ያለው ሲሆን በእንስሳት ልማት ዘርፍም ኢንቨስት በማድረግ ያለውን ከፍተኛ የእንስሳት ሀብት እና መልካም አጋጣሚዎችን በአግባቡ በመጠቀም ራሳቸውንና ሀገራቸውን እንዲጠቅሙ ሁለንተናዊ ድጋፍ ማድረግ ያስፈልጋል ፡፡

በእንስሳት ልማት ኢንቨስትመንት ካሉት መልካም ዕድሎች መካከልም የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ማዕከላትን ማቋቋም፣ የዳልጋ ከብት፣ የበግና ፍየል ራንች ማቋቋም፣ የንግሥት ንብ ብዜትና የዓሳ ጫጩት ብዜት፣ የዶሮ ቅድመ መስራች ዘር መመስረት እና የእንስሳት ምርት ማቀነባበሪያ ኢንቨስትመንቶች የሚጠቀሱ ሲሆን እነዚህን እድሎች የግል ባለሀብቱ እንዲጠቀም የቴክኒክ ድጋፎችን ማድረግ  በወሳኝነት ተግባራዊ ይሆናል፡፡

### 2.4.3 አስፈላጊ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ አዋጆች ደንቦችና መመሪዎችን ተግባራዊ ማድረግ

በእቅድ ዘመኑ የተተለሙ ግቦችና ኢላማዎችን ለማሳካት የእንስሳት ልማቱን ስኬታማ ለማድረግ የሚያግዙ ፖሊሲዎች፣ስትራቴጂዎች፣ አዋጆች፣ደንቦችና መመሪያዎች እንዲተገበሩ የሚደረግ ሲሆን በዘርፉ የሚታዩ የልማት ማነቆዎችን ለመፍታት የሚያስችሉ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችም እንዳስፈላጊነቱ የሚወጡና የሚተገበሩ ይሆናሉ፡፡ በዚሁ መሰረትም የእንስሳት ርቢ ፖሊሲና ስትራቴጂ ተቀርፆ ከዚህ ፖሊሲ የሚመነጩ አምስት የዝርያ ማሻሻል ስትራቴጂዎች የተዘጋጁ ሲሆን የርቢ፣ የወተትና የማር የግብይት ስርዓት አዋጆች እና ሌሎችም እንዳስፈላጊነቱ የሚወጡ አዋጆችና መመሪያዎች በእቅድ ዘመኑ ጸድቀው በስራ እንዲውሉ ያላሰለሰ ጥረት ይደረጋል፡፡

### 2.4.4 የፋይናንስ ም ንጮን ማስፋትና ባግባቡ መጠቀም

በቀጣይ አመታት ስትራቴጅክ እቅዱን ለመተግበር የተቀመጡ ግቦችን በማሳካት በእንስሳት ልማቱ መስክ አመርቂ ውጤት ለማስመዘገብ የፋይናንስ ምንጭን ማስፋትና የሚገኘውን ፋይናንስ ባግባቡ መጠቀም መሰረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ ከመንግስት ግምጃ ቤት የሚገኘው ፋይናንስ ውሱን መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን ይህን ወጪ ቆጣቢና ውጤታማ በሆነ መንገድ በስራ ላይ ማዋል አስፈላጊ ነው፡፡ ከዚህ ውሱን የፋይናንስ ምንጭ ባሻገር ሌሎች ለጋሽ እና አጋር ድርጅቶችን በመለየትና መልካም ግንኙነት በመፍጠር መስፈርቶቻቸውን የሚያሟሉ የፕሮጀክት ፕሮፖዛሎችን በማቅረብ የፋይናንስ ምንጭን የማስፋት ስልት እንዲሁም አሁን አብረውን ከሚሠሩ አጋሮቻችን ጋር ያለንን መልካም ግንኙነት አጠናክሮ በማስቀጠል ለውጤታማነት መትጋት ተግባራዊ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሦስት፡- የስጋት ግምገማ እና ስጋቶችን ለመቀነስ የሚተገበሩ ስትራቴጂዎች

## 3.1. የ ስጋት ግምገማ

የዘርፉን ዕቅድ ስኬታማነት ሊፈታተኑ ይችላሉ ተብለው ከሚታሰቡት ሥጋቶች መካከል ቀጥለው በቀረቡት ዋና ዋናዎቹ ላይ ትኩረት ሊደረግባቸው የሚገቡ ናቸው።

### ሀ. የግብዓት እና የመዳረሻ ገበያ እጥረት

ለበርካታ ዓመታት ለእንስሳት ምርት እና መኖ ማቀነባበሪያዎች ዝቅተኛ የአቅም አጠቃቀም አፈፃፀም ትልቁን ድርሻ የሚይዘው የግብዓት አቅርቦት ችግር (በመጠንና በጥራት ተወዳዳሪ በሚያደርጋቸው ዋጋ እና በሚፈለገው ጊዜ ውስጥ አለመገኘት) ነው። አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ የሀገራችን የእንስሳት ሀብት ልማት መጠነኛ መሻሻሎች ያሉት ቢሆንም ዕድገቱ እና ምርታማነቱ መሠረታዊ ለውጥ ያላመጣ በመሆኑ ከዘልማዳዊ ወደ ዘመናዊ እና ገበያ ተኮር እርባታ ዘዴ ሽግግር መደረግ እንዳለበት አመላካች ነው።

የኤክስፖርት ቄራዎች ግንባታ እየተስፋፋ ከመምጣቱ አንፃር እንዲሁም የተቀናጀና ወጥ የሆነ የእንስሳት አቅርቦት ስርዓት አለመኖሩና ህገወጥ የእንስሳት ንግድ እየተባባሰ መምጣቱ የእርድ እንስሳት እጥረት ሊያመጣ ይችላል። በሌላ በኩል ከፍተኛ የማምረት አቅም ያላቸው ኤክስፖርት ቄራዎች ወደ ስራ የገቡ ስለሆነ እጥረቱን የጎላ ሊያደርገው ይችላል። በአጠቃላይ ለእንስሳት ምርት እና መኖ ማቀነባበሪያዎች ጥራት ያለው ግብዓት በሚፈለገው መጠን ለማቅረብ መሠረታዊ ለውጥ ማምጣት አስፈላጊ ስለሆነ እንደሀገር ታስቦበት ሁሉም ባለድርሻ አካላት በቅንጅት ካልሰራ በስተቀር ፈታኝ ሆኖ የሚቀጥል ይሆናል።

ከዚህ በተጨማሪ አብዛኛዎቹ ኤክስፖርት ቄራዎች ምርታቸውን ወደ ሳውዲ አረቢያና ዱባይ ገበያዎች የሚልኩ በመሆኑ የመዳረሻ ገበያ ውሱንነት ይታያል። ከዚህም የተነሳ እርስ በርስ የመወዳደርና ዋጋ ቀንሶ የመሸጥ ሁኔታ ሊከሰት ይችላል። ይህም ባለሀብቱም ሆነ ሀገሪቱ ከምርቱ ሊያገኙ በሚችሉት የውጭ ምንዛሬ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ያሳድራል። ምርቶቻቸውን ለሀገር ውስጥ ገበያ የሚያቀርቡ የእንስሳት ምርት እና መኖ ማቀነባበሪያዎች ከኤክስፖርቱ ባልተናነሰ የግብዓት ችግር ያለባቸው ስለሆነ ገቢ ምርትን ለመተካት በሚደረገው ጥረት ላይ ተመሳሳይ ሁኔታዎች ሊፍጠሩ ይችላሉ።

የእንስሳት ምርታማነትን የማሳደግ እና ግብርናውን የማዘመን ሥራ በአጭር ጊዜ የሚሰራ ባይሆንም በቀጣይ አመታት መሰረት-ጣይ ተግባራት እንዲጀመሩ የችግሩን አሳሳቢነት ሁሉም ባለድርሻ አካላት እንዲያውቁት ከማድረግ ጎን ለጎን አዳዲስ የግብዓት ምንጭ እና አዳዲስ አቅራቢዎች እንዲፈጠሩ እና በእሴት ሰንሰለቱ ዉስጥ ያሉት ችግሮች (ኮትሮባንድና ህገ-ወጥ ንግድ) እንዲስተካከሉ ለማድረግ በቅንጅት የሚሰራ ይሆናል።

የዝርያ ማሻሻያ ግብዓቶች እና የፈሳሽ ናይትሮጂን መለዋወጫ ዕቃዎች ከውጭ የሚገቡ በመሆኑ እና ዋጋቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየናረ በመምጣቱ እንደ ሀገር የውጭ ምንዛር እጥረት እየጋጠመ በመሆኑ የተለያዩ ፕሮጀክቶችና ፕሮገራሞችን በመቅረፅ ፈንድ ማፈላልግና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር ግንኙነት በመፍጠር ችግሩ የመቅረፍ ሥራ ይከናወናል።የእንስሳት መኖ ማቀነባበሪያ ጥሬ ዕቃዎች ዋጋ መናር ጥራቱን የተጠበቀ መኖ ለማቀነባበር ችግር በመሆኑና በአባለ ዘር ምርት በመጠንና በጥራት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚያደርስ በመሆኑ ይህንን ችግር ለመቅረፍ የመኖ ግብዓቶችን እና የመኖ ምርት ኢንስቲትዩቱ በራሱ በአነስተኛ ወጪ የሚያመርት ይሆናል።

### ለ. በሀገር ውስጥ የእንስሳትና እንስሳት ውጤቶች ዋጋ እየጨመረ መምጣቱ

የእንስሳት ምርትና መኖ ማቀነባበሪያዎች ምርቶችን ጨምሮ አብዛኛው የሀገራችን ኤክስፖርት ምርቶች የሚጠቀሙት ግብዓቶች ምርታማነታቸው ባለማደጉ እና እየተመረተ ያለው መጠንም ከህዝባችን ቁጥር ዕድገት አንፃርም ሲመዘን ዝቅተኛ በመሆኑ ያለውን ፍላጎት የሚያሟላ ምርት ለሀገር ውስጥ ገበያ ማቅረብ ባለመቻላችን አብዛኛው ግብዓት በሀገር ውስጥ ያላቸው ዋጋ ከውጪ ገበያ ዋጋ ጋር ሲነፃፀር ከፍ ያለ ዋጋ ያለው በመሆኑ በዓለም ገበያ ውስጥ ተወዳዳሪ ሆነን እንድንቆይ አላስቻለንም።

አሁን በተጨባጭ እየታየ ካለው ነባራዊ ሁኔታ የእንስሳት ምርትና መኖ ወደ ውጭ ከሚላክበት ዋጋ በላይ በሀገር ውስጥ ገበያ የሚሸጥበት ሁኔታ እየጨመረ መምጣቱ በውጭ ንግዱ ላይ ተፅዕኖ በማሳደር የተወሰኑት ላኪዎች ምርታቸውን በብዛት ለሀገር ውስጥ ገበያ የማቅረብ ዝንባሌ ሊያሳዩ ይችላሉ። ይህ በዚህ ሁኔታ የሚቀጥል ከሆነ ሀገሪቷ ከንዑስ ዘርፉ ማግኘት ያለባትን የውጪ ምንዛሬ እንዳታገኝ ስለሚያደርግ ችግሩን ለመቅረፍ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት መከናወን ያለባቸው ተግባራት ለይቶ ማከናወን ያስፈልጋል።

### ሐ) ዓለም አቀፍ የምግብ ጥራት መስፈርት ማሟላት አለመቻል

በኢኮኖሚ የበለፀጉ ሀገራት ለሕዝባቸው ጤንነት ሲሉ የእንስሳት ውጤቶች የሚገዙበት መስፈርት በጣም ከፍ እያለና እንዲሁም መስፈርቱን ከሚያሟሉ ያደጉ ሀገሮች የመግዛት ዝንባሌ ከመቼውም ጊዜ የበለጠ እየተጠናከረ ነው። የዓለም ገበያ በሚፈልገው የጥራት ደረጃ ምርቶቻችንን የመላክ አቅም በመፍጠር ተወዳዳሪ ለመሆን መጣር ወሳኝ እየሆነ መጥቷል። ስለሆነም የሀገራችን የተቀነባበሩ የእንስሳት ምርት ውጤቶች ዓለም አቀፍ የጥራት ደረጃዎችን በማሟላት በገበያ ተወዳዳሪ እንዳይሆኑ ከዳረጉት ምክንያቶች መካከል ከበሽታ ነፃ (Disease Free Zone) አካባቢን ያለመለየት እንዲሁም እንስሳው ከተወለደበት ጊዜ ጀምሮ የሚያስረዳ (Traceability) የመረጃ ስርዓት ያለመዘርጋቱ ዋና ዋናዎቹ ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ የዓለም የእንሰሳት ኢንዱስትሪ ምርት ገበያ በርካታ የምርት ስብጥር ያላቸው ሀገሮች የሚሳተፉበት ስለሆነ አሁን በሀገራችን በሚገኙ ማቀነባበሪያዎች እየተመረተ ያለው ምርት ስብጥር ለዚህ ውድድር የማያበቃን በመሆኑ ይህንንም ለማሻሻል ከፍተኛ ቴክኖሎጂ፣ ዕውቀት እና ክህሎት ስለሚፈልግ ፈታኝ ሆኖ ሊቀጥል ይችላል የሚል ሥጋት አለ።

### መ. ዘርፉን ሊደግፍ የሚችል ልምድና ክህሎት ያለው ባለሙያ ማፍራት ያለመቻል

የቴክኖሎጂ ሽግግር፣ ምርጥ ተሞክሮዎችን ሊቀምርና ሊያስፋፋ የሚችል፣ በእንስሳት ምርትና መኖ ማቀነባበር የሰለጠነ ባለሙያ በሀገር ውስጥ ባሉት ዩኒቨርሲቲዎች ትኩረት ሰጥቶ ማፍራት ያለመቻል እና ለእንስሳት ምርቶቻችን በዓለም ዓቀፍ ገበያ የመደራደር ክህሎትና ልምድ ያለው ባለሙያ በገበያ ላይ ያለማግኘት በትግበራው ሂደት ከሚፈታተኑን ሥጋቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ ናቸው። በገበያ የመደራደር ዕውቀት ብቻ ሳይሆን የእንስሳት ምርትና መኖ ማቀነባበሪያዎቻችን በገበያ ላይ ተፈላጊነት ያለውን ምርት እንዲያመርቱ እና እሴት እንዲጨምሩ የቴክኒካል ድጋፍ የሚሰጡ ባለሙያዎች በተፈለገው ደረጃ ባለመኖራቸው በዕቅዱ አፈፃፀም ላይ የራሱ የሆነ አሉታዊ ተፅእኖ ስለሚያሳድር እቅዱ ይህንን ሊቀርፍ በሚችል አግባብ መሆን እንዳለበት ግንዛቤ ተወስዷል።

## 3.2. ስጋቶችን ለመቀነስ የሚያስችሉ ስትራቴጂዎች

### ሀ. የእርድ እንስሳት እጥረትን በተመለከተ

የእንሰሳት አቅርቦት እጥረቱን ለመቅረፍ በአርብቶ አደር አካባቢ ያሉትን እንስሳት ወደ ጎረቤት ሀገሮች የሚገቡበትን መንገድ በመለየት፣ የቁም እንስሳት ግብይት ስርዓት አዋጅ እና ደንብ በመተግበር፣ ሕገወጥ የቁም እንስሳት ንግድን

ለማስቆም የሚያስችል ቅንጅታዊ ሥራ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሥራት እንዲሁም ከዚህ በፊቱ በተሻለ ደረጃ በግብዓት የገበያ ትስስር በመፍጠር በጊዜያዊነት የሚፈጠረውን የእንስሳት አቅርቦት ችግሮችን ለመቅርፍ ይሰራል። ይህ ከአጭር ጊዜ አንፃር በአቅርቦት በኩል የሚከሰተውን ስጋት ለመቅረፍ የተቀመጠ ስልት ሲሆን ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት ከረጅም ጊዜ አኳያ ከሌሎች ባለለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት የእንስሳት እርባታ ዘዴው እንዲዘምንና ኤክስፖርት ቄራዎች የራሳቸው የሆነ እንስሳት አቅርቦት እንዲኖራቸው በራንች ኢንቨስትመንት ላይ እንዲሰማሩ እንዲሁም ሌሎች ባለሃብቶች በእንስሳት እርባታው ዘርፍ እንዲሰማሩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የሚሰራ ይሆናል። በዚህ በተጨማሪ የኤክስፖርት እንስሳት ምንጭ የሆኑ አካባቢዎችን ለይቶ ለአርቢዎች የሚሰጠውን የኤክስቴንሽን ድጋፍ እንዲሁም የዝርያ ማሻሻል፣ የመኖና የጤና አጠባበቅ ስልቶች ላይ ትኩረት በማድረግ በህብረት ሥራ ማህበራት እንዲደራጁ በማድረግ የገበያ ትሥሥር ሥርዓቱን ማጠናከርና ባለሀብቶች እነዚህ አካባቢዎች ላይ የራሳቸው ራንች እንዲኖራቸው ምቹ ሁኔታ በማፍጠር በአውትግሮዌር እና በኮንትራት ፋርሚንግ ስልት አቅርቦት ማነቆ መፍታት የሚያስችል ሥራ መሥራት ይጠበቃል።

## ለ. የማር ኢንዱስትሪ ግብዓት እጥረትን በተመለከተ

የሀገራችን የማር ኢንዱስትሪ ምርት በትላልቅ የዓለም ገበያዎች እየተፈለገ የመጣ ቢሆንም በዘርፉ ያለው ግብዓት በመጠንም ሆነ በጥራት በቂ ካለመሆኑ የተነሳ የማር ምርት በማቀነባበር ላይ የተሰማሩ ባለሀብቶች የደንበኞቻቸውን የምርት ፍላጎት ለማሟላት ሲቸገሩ ተስተውሏል። በቀጣዩ የሦስት አመት ዕቅድ ዘመንም ይህ ችግር ዘርፉን እንዳይፈታተነው በእሴት ሰንሰለቱ ውስጥ ተዋንያን ከሆኑ አካላት እና ከሌሎች ባለድርሻዎች ጋር በመሆን የማርና ሰም ማቀነባበሪ ባለቤቶች በተከለሉ ደኖች አካባቢ የራሳቸው ዘመናዊ የንብ ማነቢያ ማዕከል እንዲኖራቸው ድጋፍ ይደረጋል።

እምቅ የማር ምርት ባላቸው ክልሎችን ለይቶ በዚህ አካባቢ የሚገኙ ማህበራትና ዩኒየኖችን ከማርና ሰም ማቀነባበሪያ ካምፓኒዎች ጋር የተጀመረውን የማስተሳሰር ሥራ አጠናክሮ ማስቀጠል ተገቢ ይሆናል። ከዚህ በተጨማሪ በተፋሰስ የለሙና የተከከሉ አካባቢዎችን ማዕከል በማድረግ በአካባቢው ያሉት አርሶ አደሮች በተለይም ሴቶችና ወጣቶች በጥቃቅንና አነስተኛ በንብ ማነብ ሥራ እንዲሰማሩ በማድረግ ከማርና ሰም ማቀነባበሪያዎች ጋር የማስተሳሰር ተግባር ይከናወናል።

## ሐ. የወተትና ወተት ዉጤቶች በተመለከተ

በወተት ዘርፉ ኢንዱስትሪው የተስተዋሉ ዋና ዋና ችግሮችን ቅድሚያ ሰጥቶ ለመፍታት የሚያስችሉ አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ የጥሬ ወተት፣ ሌሎች የግብዓት አቅርቦትን፣ የእሴት ሰንሰለቱ የሎጀስቲክስ ማነቆችን መፍታት፣ የወተት ጥራትና ደህንነት ማሻሻል፣ በወተት ግብይት ሰንሰለት ውስጥ የሚታዩትን የአቅርቦትና ፍላጎት ያለመጣጣም ክፍተት መፍታት በዋናነት ትኩረት ተደርጎ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የሚሰራ ይሆናል።

## መ. የመዳረሻ ገበያ ውስንነትን በተመለከተ

ከዓለም የሥጋ ገበያ ተለዋዋጭነት ጋር ተያይዞ የሚፈጠረውን የገበያ እጥረት ለመቅረፍ አስቀድሞ በዕቅድ ዘመኑ ታሳቢ የተደረጉ አማራጭ ገበያዎችን መያዝ፣ እንዲሁም የምርት ጥራት እና መጠን በበቂ ሁኔታ በማሻሻል እና ያለውን የግንኙነት አድማስ በማስፋት አሁን በመካከለኛው ምስራቅ ሀገራት ያሉትን የሥጋ ደንበኞች ቁጥር ለማሳደግ በመስራት ሊከሰት የሚችለውን የመዳረሻ ገበያ ውስንነት መከላከል የሚቻል ይሆናል።

የእንስሳት ምርትና መኖ ማቀነባበሪያዎች ዓለም ዓቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ምርት እንዲያመርቱ በመደገፍና የምርት ጥራትና ደረጃን በማሻሻል ለደንበኞች ማስተዋወቅ ተገቢ ይሆናል።

### ሠ. የአቅም ግንባታ ክፍተትን በተመለከተ

አሁን በሀገራችን በዝርያ ማሻሻል፣ በምግብ ሳይንስና አግሮፕሮሰሲንግ ላይ ሥርዓተ-ትምህርት ቀርፀው ትምህርት የሚሰጡ ዩኒቨርሲቲዎች እና የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት ዘርፉን የሚደግፉ የትምህርት ክፍሎች እንዲከፈቱ እና የኢንዱስትሪ ዩኒቨርስቲ ትስስሩ እንዲጠናከር ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

የቁርኝት ፕሮግራምና የሌሎች ሀገራት ልምድና ምርጥ ተሞክሮ በመቀመር በእንስሳት ምርትና መኖ ማቀነባበሪያዎች ለማስፋፋት፣ የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችን ለማሸጋገር እንዲሁም የዘርፉን ልማት ሊደግፍ የሚችል ልምድና ክህሎት ያለው ባለሙያ በገበያው ላይ እንዲኖር በማድረግ ሊከሰት የሚችለውን ስጋት ለመቅረፍ ይሰራል፡፡ አሁን በFSRP ፕሮጀክት ድጋፍ የተጀመረውን የብሔራዊ ወተት ሀብት ልማት ሥልጠና ማዕከል ግንባታ ክትትል በማድረግ እንዲጠናቀቅ በማድረግ ጥራቱን የጠበቀ ዕውቀትና ክህሎት ሽግግር ማዕከል እንዲሆን በትጋት ይሠራል፡፡

# ክፍል አራት : የክትትልና ግምገማ ስርዓት

የቀጣይ አሥር ዓመታት ዕቅድን ለመተግባር አፈጻጸምን በመረጃ ሥርዓት ላይ የተመረኮዘ በማድረግ ጠንካራ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል፡፡ የክትትልና ግምገማ ዋንኛ ዓላማ የተዘጋጀውን ስትራቴጂ በየጊዜው እየፈተሹ እንደ አስፈላጊነቱ ማሻሻያ ለማድረግና ከተቀመጡ ስትራቴጂያዊ ግቦች፣ የአፈጻጸም መለኪያዎችና ዒላማዎች አንጻር የሚጠበቁ ውጤቶች መገኘታቸውን በአፈጻጸም ስኬት አመልካች መለኪያዎች አማካይነት ፈትሾ በአፈጻጸም ለታዩ ችግሮች መፍትሔ በመስጠት ወደ ሚፈለገው የመጨረሻ ግብ መድረስ ነው፡፡

በተቋም ደረጃ ለሚካሄደው ግምገማ አጠር ያለ ዕቅድ ማዘጋጀት የሚያስፈልግ ሲሆን ይህም የሚገመገው ምን እንደሆነ፣ በማን እና መቼ እንደሚገመገም፣ የግምገማው ውጤትም ለማን ሪፖርት እንደሚደረግ የሚያሳይ ይሆናል፡፡

ለክትትልና ግምገማው ተግባራዊነት የእንስሳት ዝርያ ማሻሻል፣ ምርትና መኖ ማቀነባበሪያ ኢንቨስትመንትና ኢንዱስትሪዎች አፈጻጸም መረጃ በሚዘጋጀው የመረጃ ስርዓት እና በሚቀመጠው መርሃ ግብር መሰረት ወቅቱን ጠብቆ የሚሰበሰብ ሲሆን ከደንበኞችና ባለድርሻ አካላት ጋር የሩብ ዓመትና ዓመታዊ ግምገማዎች ይካሄዳሉ፡፡

የክትትልና ግምገማ ስራዎች በሪፖርት፣ በሱፐርቭዥንና በአካል ግምገማ የሚካሄዱ ሲሆን ሳምንታዊ ወርሃዊ፣ የሩብ ዓመትና ዓመታዊ ግምገማዎች በማካሄድ ሪፖርቶች ተዘጋጅተው ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ይቀርባሉ፡ ፡ የተለያዩ ስራዎችና ፕሮጀክቶች ሱፐርቭዥን ስራዎች በተቋሙ አመራሮችና ባለድርሻ አካላት የሚካሄድ ሲሆን በዚሁ መሰረት በአፈጻጸም ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታት ግብረ-መልስ በመስጠት የአፈጻጸም ክትትል ይደረጋል፡፡

ከላይ በተጠቀሰው መሰረት የክትትልና ግምገማ ስርዓቱ ለስትራቴጂው አፈጻጸም የሚገባውን ሚና መጫወት እንዲችል ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ተቋማዊ አደረጃጀትን የመፍጠር፣ ተገቢውን የሰው ሀይልና በጀት መመደብና ባሙያዎችን በማብቃት የክትትልና ግምገማ አቅም እንዲያድግ ይደረጋል፡፡

# ክፍል አምስት፡- አባሪዎች

| ግቦች እና ዋና ዋና ዝርዝር ቁልፍ የአፈጻጸም አመልካቾች | መለኪያ | የ2012 አፈጻጸም (መነሻ) | የ2012-2022 ዓመታዊ ኢላማዎች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | 2019 | 2020 | 2021 | 2022 |
| **ግብ 1 የእንስሳት ዝርያ ማሻሻል** | | | | | | | | | | | | |
| የተቋቋመ የዳልጋ ከብት የብዜት ማዕከላት | በቁጥር | | | | | | | 1 | 1 | 1 | | |
| በማህበረሰብ አቀፍ የበግና ፍየል እርባታ ተጠቃሚ አርሶ/አርብቶ አደር | በመቶኛ | 20 | 22.00 | 24.20 | 26.62 | 28.04 | 30.84 | 33.92 | 37.31 | 41.04 | 46.14 | 51.00 |
| የአውራ በግ አቅርቦትና ሥርጭት | በቁጥር | 3811 | 4234 | 4705 | 5227 | 5808 | 6389 | 7028 | 7730 | 8,503 | 9354 | 10289 |
| የአውራ በግ አቅርቦትና ሥርጭት | በቁጥር | 953 | 1059 | 1176 | 1307 | 1452 | 1597 | 1757 | 1933 | 2126 | 2339 | 2572 |
| በማህረሰብ አቀፍ የበግና ፍየል እርባታ ፕሮግራም የአርሶ/አርብቶ አደር ተሳትፎ | በቁጥር | 20 | 22 | 24.2 | 26.6 | 29.3 | 32.2 | 35.4 | 38.9 | 42.8 | 47.1 | 51.8 |
| ዝርያቸው የተሻሻለ የወተት ላሞች | በቁጥር | 571,341 | 657,042 | 755,598 | 868,938 | 999,279 | 1,149,171 | 1,321,547 | 1,519,779 | 1,747,746 | 2,009,908 | 2,311,394 |
| የተሻሻሉ የወተት ላሞች የተጠቀሙ አርሶ/ አርብቶ አደሮች | በ% | 28 | 30% | 32% | 35% | 38% | 40% | 44% | 47% | 51% | 55% | 59% |
| ዲቃላ የወተት ላም (Crossbreed) የቀን ወተት ምርት | ሊት/እንስሳ | 6 | 6.36 | 6.74 | 7.15 | 7.57 | 8.03 | 8.51 | 9.02 | 9.56 | 10.13 | 10.74 |
| ንፁህ የውጪ ዝርያ (Exotic) ቀን ወተት ምርት | ሊት/እንስሳ | 13.07 | 13.41 | 13.76 | 14.13 | 14.5 | 14.88 | 15.27 | 15.68 | 16.09 | 16.51 | 16.95 |
| በጊደር ማራቢያ ማዕከላት የሚወለዱ ጥጆች | በቁጥር | | 0 | 30 | 150 | 200 | 250 | 275 | 300 | 325 | 350 | 400 |
| በተሻሻሉ ኮርማት፣ በስንክሮናይዜሽን፣ ፆታው በተለየ አባላዘር በማዳቀል እና በመደበኛ ድቀላ በማህበረሰቡ የሚወለዱ የጥጆች | በቁጥር | 510,300 | 567,000 | 630,000 | 700,000 | 770,000 | 847,000 | 931,700 | 1,024,870 | 1,127,357 | 1,240,093 | 1,364,102 |
| የመስክ ማዳቀል አገልግሎት ውጤታማነት | በቁጥር | 2.27 | 2.23 | 2.2 | 2.16 | 2.13 | 2.09 | 2.06 | 2.02 | 1.99 | 1.95 | 1.91 |
| የተቋቋመ የኮርማ አገልግሎት ጣቢያዎችን | በቁጥር | | | | | 4 | 4 | 6 | 6 | 11 | 11 | 12 |
| የተቋቋመ የአሳ ብዜት ማዕከላት | በቁጥር | 2 | | | | | | 2 | 3 | 3 | 3 | 4 |
| የተቋቋመ የቅድመ መስራች ዘር/ grand parentstock | በቁጥር | | | | | | | | | 1 | | |
| የተቋቋመ የንግሥት ንብ ብዜትና ማሰልጠኛ ማዕከል | በቁጥር | 5 | | | | | | | | 1 | | |
| የተሻሻለ የንብ ዝርያ ስርጭት | በቁጥር | 68 | | | | | 90 | 95 | 110 | 115 | 130 | 140 |

| ግቦች እና ዋና ዋና ዝርዝር ቁልፍ የአፈጻጸም አመልካቾች | መለኪያ | የ2012 አፈጻጸም (መነሻ) | የ2012-2022 ዓመታዊ ኢላማዎች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | 2019 | 2020 | 2021 | 2022 |
| ተሻሻሉ የንብ መኖ ችግኝ ሥርጭት | በቁጥር | 46,000 | | | | | 25000 | 25000 | 25000 | 25000 | 25000 | 25000 |
| **ግብ 2. ግበዓት አቅርቦት እና ስርጭትን ማሳደግ** | | | | | | | | | | | | |
| ዝርያቸው የተሻሻሉ የአባለዘር አምራች ኮርማዎች አቅርቦት | ቁጥር | 47 | 54 | 62 | 71 | 82 | 94 | 108 | 124 | 143 | 164 | 189 |
| በእንስቲትዩቱ የአባለዘር ምርትና ስርጭት | በዶዝ | 1,457,440 | 1,734,080 | 1,850,240 | 2,205,920 | 2,640,640 | 2,714,880 | 3,068,160 | 3,100,480 | 3,351,360 | 3,881,280 | 4,369,280 |
| በክልሎች አባለዘር ምርትና ስርጭት | በዶዝ | 400,000 | 400,000 | 600,000 | 600,000 | 600,000 | 1,000,000 | 1,200,000 | 1,800,000 | 2,300,000 | 2,600,000 | 3,100,000 |
| ፈሳሽ ናይትሮጂን ምርትና ስርጭት | በዶዝ | 287,000 | 326,606 | 371,678 | 422,970 | 481,340 | 547,765 | 623,357 | 709,380 | 807,274 | 818,678 | 931,656 |
| ፆታው የተለየ አባላዘር (sexed semen) | በዶዝ | 15,000 | 18,000 | 21,600 | 25,920 | 31,104 | 37,325 | 44,790 | 53,748 | 64,498 | 77,398 | 92,878 |
| ድራት ሆርሞን (Heat synchronization) | በዶዝ | 16,000 | 19,200 | 23,040 | 27,648 | 33,178 | 39,814 | 47,777 | 57,332 | 68,798 | 82,558 | 100,000 |
| የመስራች ዘር (parent stock) አቅርቦት | ቁጥር | | | 300,000 | 305,000 | 310,000 | 315,000 | 320,000 | 325,000 | 330,000 | 335,000 | 340,000 |
| **ግብ 3. የተቀነባበረ የእንስሳት ምርትና መኖ ፤ ጥራት፤ደህንነት እና ምርታማትን ማሳደግ** | | | | | | | | | | | | |
| የእንስሳት ምርትና መኖ ማቀነባበር ኤክስፖርት የውጭ ምንዛሪ ግኝት | ሚ.ዶ | 72.48 | 82.78 | 119.19 | 96.93 | 89.71 | 124.31 | 128.04 | 131.88 | 135.84 | 139.91 | 143.49 |
| ተቀነባብሮ ለዉጪ ገበያ የቀገረበ የበግና ፍየል ሥጋ ምርት | ቶን | 11,438 | 13,269 | 17,204 | 11,257 | 10,202 | 16,500 | 16,995 | 17,504 | 18,030 | 18,570 | 19,128 |
| | ሚ.ዶ | 64.85 | 72.71 | 104.29 | 82.1 | 74.23 | 99.00 | 101.97 | 105.03 | 108.18 | 111.43 | 114.77 |
| ተቀነባብሮ ለዉጪ ገበያ የቀረበ የዳልጋ ከብት ሥጋ ምርት | ቶን | 380.75 | 226 | 359.15 | 0.0 | 15.1 | 150 | 155 | 159 | 164 | 169 | 174 |
| | ሚ.ዶ | 1.33 | 0.79 | 1.44 | 0 | 0.07 | 0.52 | 0.54 | 0.55 | 0.57 | 0.59 | 0.60 |
| ለዉጪ ገበያ የቀረበ የእርድ ተረፈ ምርት | ቶን | 2,461.89 | 2,304 | 5125.35 | 4462.3 | 3025.8 | 5865 | 6041 | 6222 | 6409 | 6601 | 6799 |
| | ሚ.ዶ | 3.33 | 5.62 | 13.41 | 11.6 | 9.01 | 13.00 | 13.39 | 13.79 | 14.21 | 14.63 | 15.07 |
| ለዉጪ ገበያ የቀረበ የተቀነባበረ ማር ምርት | ቶን | 150.09 | 17 | 53.91 | 45 | 29 | 100 | 103 | 106 | 109 | 113 | 116 |
| | ሚ.ዶ | 0.52 | 0.07 | 0.22 | 0.28 | 0.315 | 0.60 | 0.62 | 0.64 | 0.66 | 0.68 | 0.70 |
| ለዉጪ ገበያ የቀረበ የሰም ምርት | ቶን | 235.01 | 229 | 158.02 | 145.4 | 164 | 150 | 155 | 159 | 164 | 169 | 174 |
| | ሚ.ዶ | 2.09 | 1.76 | 1.16 | 1.15 | 1.26 | 1.54 | 1.59 | 1.63 | 1.68 | 1.73 | 1.79 |

| ግቦች እና ዋና ዋና ዝርዝር ቁልፍ የአፈጻጸም አመልካቾች | መለኪያ | የ2012 አፈጻጸም (መነሻ) | የ2012-2022 ዓመታዊ ኢላማዎች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | 2019 | 2020 | 2021 | 2022 |
| ለዉጪ ገበያ የቀረበ የዓሳ ምርት | ቶን | 373.56 | 313 | 31.10 | 34.1 | 32 | 685 | 706 | 727 | 749 | 771 | 794 |
| | ሚ.ዶ | 0.04 | 0.06 | 0.01 | 0.01 | 0.01 | 0.24 | 0.25 | 0.26 | 0.26 | 0.27 | 0.28 |
| ለውጭ ገቢያ የቀረበ የዶሮ ምርት | ቶን | 0.00 | 55 | 123.22 | 0 | 130 | 178.9 | 184 | 190 | 195 | 201 | 207 |
| | ሚ.ዶ | 0.00 | 0.28 | 0.54 | 0 | 0.52 | 0.57 | 0.59 | 0.60 | 0.62 | 0.64 | 0.66 |
| ዉጪ ገበያ የቀረበ የቀረበ መኖ | ቶን | 204 | 4,595 | 0.00 | 6005.2 | 4000 | 11686 | 12037 | 12398 | 12770 | 13153 | 13547 |
| | ሚ.ዶ | 0.09 | 1 | 0.00 | 1.54 | 4.00 | 9.00 | 9.27 | 9.55 | 9.83 | 10.13 | 10.43 |
| ለውጭ ገቢያ የሚቀርብ የተቀነባበረ ወተትና የወተት ተዋጽኦ | በሚ.ሊትር | 0.77 | 1.18 | 0.81 | 1.12 | 4.51 | 4.71 | 4.85 | 5.00 | 5.15 | 5.30 | 5.46 |
| | ሚ.ዶ | 0.12 | 0.12 | 0.10 | 0.18 | 0.36 | 0.39 | 0.41 | 0.42 | 0.43 | 0.44 | 0.46 |
| ተቀነባብሮ ለሀገር ውስጥ ገበያ የሚቀረብ ወተት ምርት መጠን | በሚ.ሊ | 105.7 | 124 | 130.2 | 136.71 | 143.54 | 150.72 | 158.26 | 166.17 | 174.48 | 183.20 | 192.36 |
| ተቀነባብሮ ለሀገር ውስጥ ገበያ የቀረበ የመኖ ምርት መጠን ዕድገት | በቶን | 135,232 | 160,000 | 180,000 | 200,000 | 291,870 | 321,057 | 342,165 | 342,165 | 342,165 | 342,165 | 342,165 |
| ተቀነባብሮ ለሀገር ውስጥ ገበያ የቀረበ የዶሮ ሥጋ ምርት መጠን ዕድገት | በቶን | 150 | 4284 | 4712.4 | 5183.64 | 2,100.00 | 2,400.00 | 2,700.00 | 2,700 | 3,300 | 3,600 | 3,600 |
| የቤተ-ሙከራ እውቅና /Accredited ያገኙ የእንስሳት ምርት እና መኖ ማቀነባበሪያዎች | የፋብሪካ ቁጥር | | 1 | 2 | 2 | 3 | 3 | 4 | 4 | 5 | 5 | 5 |
| የእንስሳት ምርት ማቀነባበሪያዎች የምግብ ደህንነት አስተዳደር ስርዓት ISO 22000፡2018 የተገበሩ ፋብሪካዎች | የፋብሪካ ቁጥር | 12 | 13 | 14 | 15 | 17 | 19 | 21 | 24 | 26 | 28 | 32 |
| የተገነባ የእንስሳት ምርት እና መኖ ማቀነባበሪያ ጥራት ፍተሻ ላቡራቶሪ | በቁጥር | | | | | | | | | 1 | | |
| የተደረገ የእንስሳት ምርትና መኖ ጥራት ፍተሻና ትንተና | በናሙና ቁጥር | 150 | | | | 200 | 250 | 300 | 300 | 300 | 300 | 300 |
| የተገነባ ዘመናዊ/ሞዴል የእንስሳት እርባታና ማቀነባበሪያ | በቁጥር | | | | | | | | 1 | 1 | 1 | 2 |
| በመኖ ሰርቶ ማሳያ የለሙ ተሻሻሉ የመኖ እፅዋቶች | በቶን | | | | 20 | 35 | 95 | 95 | 95 | 95 | 95 | 95 |

| ግቦች እና ዋና ዋና ዝርዝር ቁልፍ የአፈጻጸም አመልካቾች | መለኪያ | የ2012 አፈጻጸም (መነሻ) | የ2012-2022 ዓመታዊ ኢላማዎች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | 2019 | 2020 | 2021 | 2022 |
| አለም አቀፍ ምርጥ ተሞክሮ ካላቸው ሀገራት ጋር የተፈጠረ ቁርኝት | ሀገራት በቁጥር | | | | | | | | | | 1 | 1 |
| **ግብ 4 የጥናት፤ ምርምር እና ስርፀትን ማሳደግ** | | | | | | | | | | | | |
| የተካሄደ ችግር ፈቺ ጥናትና ምርምር | በቁጥር | 4 | | | | | 4 | 4 | 5 | 5 | 6 | 6 |
| የታተመ ጥናትና ምርምር | በቁጥር | 4 | | | | | | 1 | 1 | 1 | | 1 |
| የተካሄደ ምርት አዋጭነት / Economical production/ እና ቴክኖሎጂዎች ተጽዕኖ ግምገማ | በቁጥር | | | | | | 5 | 5 | 5 | 6 | 7 | 7 |
| **ግብ 5 ኢንቨስትመንትና ገበያን ማስፋፋት** | | | | | | | | | | | | |
| በዘርፉ የተሰቡ አዳዲስ ኢንቨስትመንቶች | በቁጥር | 7 | 3 | 4 | 4 | 5 | 5 | 5 | 6 | 6 | 6 | 6 |
| ወደ ስራ የገቡ ኢንቨስትመንቶች | በቁጥር | 13 | 3 | 2 | 3 | 4 | 4 | 5 | 5 | 5 | 6 | 6 |
| የተፈጠሩ አዳዲስ የውጭ መዳረሻ ገበያዎች | በቁጥር | 4 | | | | | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | |
| የርቢ፣የወተት፣ የማርና ሰም የግብይት አዋጅ ማፀደቅ | በቁጥር | | | | | | 3 | | | | | |
| የተቋቋመ የራንች ኢንስትመንት | በቁጥር | | | | | | | 1 | 2 | 1 | 2 | |
| የተዘጋጀ የእርድ እንስሳት ግብይት መመሪያ | በቁጥር | | | | | | 1 | | | | | |
| **ግብ 6 የእንስሳት ዝርያ ማሻሻል፣ ምርት እና ተዋፅኦ ማቀነባበር መረጃ ማሳደግ** | በቁጥር | | | | | | | | | | | |
| የተቋቋመ የአነስተኛ አመንዣኪ እንስሳት መረጃ ቋት | | | | | | | 1 | | | | | |
| የተመዘገበ አነስተኛ አመንዣኪ እንስሳት ምርታማነት መረጃ | በቁጥር | | | | | | 45,000 | 55,000 | 13,000 | 20,000 | 25,000 | 30,000 |
| አዲስ የተመዘገበ የወተት ከብት እርባታ | በቁጥር | 4106 | 1,000 | 600 | 600 | 1400 | 2000 | 2500 | 3000 | 3500 | 4000 | 5000 |

| ግቦች እና ዋና ዋና ዝርዝር ቁልፍ የአፈጻጸም አመልካቾ | መለኪያ | የ2012 አፈጻጸም (መነሻ) | የ2012-2022 ዓመታዊ ኢላማዎች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | 2019 | 2020 | 2021 | 2022 |
| የተመዘገበ የወተት ከብት ምርታማነት መረጃ | በቁጥር | 83311 | 100,000 | 110,000 | 120,000 | 135,000 | 140,000 | 150,000 | 150000 | 160000 | 170000 | 180000 |
| የተመረመረ የወተት ንጥረ ነገር ይዘት ናሙና | በቁጥር | | | 3,000 | 3,000 | 3000 | 3200 | 3500 | 4000 | 5000 | 6000 | 7000 |
| የተለካ የሶማቲክ ሴል (SCC) በናሙና | በቁጥር | | | | 3,000 | 3000 | 3200 | 3500 | 4000 | 5000 | 6000 | 7000 |
| የተካሄደ የእንስሳት ዘረመል ምርመራ በናሙና | በቁጥር | 6787 | 600 | 3,000 | | 2500 | 2500 | 2500 | | | | |
| የተካሄደ የእንስሳት ዝርያ መረጃ ትንተና (EBV) | በሳምንት | | | | | 4 | 4 | 4 | 6 | 4 | 4 | 4 |
| ለአርቢው የተሰጠ ግብረ መልስ | በቁጥር | 52 | 52 | 52 | 104 | 104 | 104 | 104 | 104 | 104 | 104 | 104 |
| የእርድ እንስሳት ግብይት እሴት ሰንሰለት ዲጂታል የገበያ መረጃ ስርዓት ዝርጋታ | በቁጥር | | | | | | 1 | | | | | |
| **ግብ 7. ቴክኖሎጂ ማሸጋገር፣ማላመድና ማስረፅ** | | | | | | | | | | | | |
| በእንስሳት ዝርያ ማሻሻል የተላመደና የተሰረፀ ቴክኖሎጂ | | | | | | | | 1 | 1 | 1 | 1 | 2 |
| በእንስሳት ምርት ማቀነባበር ምርታማነት የተላመደና የተሰረፀ ቴክኖሎጂ | | | | | | | | 1 | 1 | 1 | 1 | 2 |
| **ግብ 8 የዘርፉን የሰው ሀይል አቅም መገንባት** | | | | | | | | | | | | |
| የሰለጠኑ አዳቃይ ቴክኒሺያኖች | ቁጥር | 31 | | | | 600 | 600 | 600 | 600 | 600 | 600 | 600 |
| የተሃድሶ ስልጠና የተሰጣቸው የአዳቃይ ተክኒሽያንኖች | ቁጥር | 510 | | | | 50 | 50 | 50 | 50 | 50 | 50 | 50 |
| የሰለጠኑ የፈሳሽ ናይትሮጂን ኦፕሬተሮች | ቁጥር | 20 | | | | 26 | 30 | 35 | 35 | 35 | 35 | 35 |
| የሰለጠኑ የአባላዘር ላብራቶሪ ቴክኒሽያኖች | ቁጥር | 15 | | | | 15 | 15 | 15 | 15 | 15 | 15 | 15 |

| ግቦች እና ዋና ዋና ዝርዝር ቁልፍ የአፈጻጸም አመልካቾች | መለኪያ | የ2012 አፈጻጸም (መነሻ) | የ2012-2022 ዓመታዊ ኢላማዎች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | 2019 | 2020 | 2021 | 2022 |
| በማሽነሪ ጥገና የሰለጠኑ ባለሙያች | ቁጥር | - | | | | 3 | **3** | **3** | 3 | 3 | 3 | 3 |
| የሰለጠኑ የመረጃ መዝጋቢ ባለሙያዎች | ቁጥር | 20 | | | | 70 | 80 | 90 | 110 | 120 | 150 | 160 |
| የወተት ከብት አርቢዎች ስልጠና ማካሄድ | ቁጥር | - | | | | 600 | 700 | 800 | 1500 | 2000 | 3000 | 4000 |
| ለማቀነባበርያ ፋብሪካ ባለሙያዎች የተሰጠ ስልጠና | ቁጥር | 400 | | | | 569 | 683 | 819 | 819 | 819 | 819 | 819 |
| በቁርኝት የተሰለጠኑ MSc ባለሙያች | ቁጥር | | | | | 8 | 8 | 8 | 9 | 9 | 12 | 12 |
| በቁርኝት የተሰለጠኑ PhD ባለሙያች | ቁጥር | | | | | 3 | 3 | 4 | 5 | 5 | 6 | 6 |
| **ግብ 9 ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ማሻሻል** | ቁጥር | | | | | | | | | | | |
| የቀነሰ የሙቀት አማቂ ጋዝ መጠን | ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን | 12.06 | | | | | 21.6 | | | | | 48 |
| በኢንስቲትዩቱና በምርት ማቀነባበሪያዎች የተቋቋመ የባዮጋዝ ፕላንት | ቁጥር | 1 | | | | | 2 | 3 | 6 | 6 | 7 | 7 |
| በእንስሳት ምርት ማቀነባበሪያዎች የተገነባ የፈሳሽ ቆሻሻ ማጣሪያ ፕላንት | ቁጥር | 2 | | | | | 1 | 1 | 2 | 2 | 3 | 3 |
| የአከባቢ ጥበቃ አስተዳዳር ስርዓት የተተገበሩ የሥጋ ማቀነባበሪያዎች | በቁጥር | 1 | | | | | | 2 | 2 | 3 | 3 | 4 |
| የአከባቢ ተፅዕኖ ቅነሳ የተተገበሩ ፋብሪካዎች | በቁጥር | | | | | | 9 | 9 | 10 | 10 | 10 | 8 |
| በጥቅሉ የተፈጠር የሥራ ፅድል | በቁጥር | | 3,323.58 | 4,432.18 | 5,500.00 | 6,331 | 9,697 | 12,369 | 15,388 | 18,407 | 21,426 | 24,445 |
| በቋሚነት የተፈጠረ የስራ ዕድል | በቁጥር | 2812 | 1,064.74 | 1,420.45 | 2,000.00 | 2,029 | 3,107 | 3,963 | 4,930 | 5,897 | 6,864 | 7,831 |
| በጊዜያዊነት የተፈጠረ የስራ ዕድል | በቁጥር | 1108 | 2,258.84 | 3,011.73 | 3,500.00 | 4,302 | 6,590 | 8,406 | 10,458 | 12,510 | 14,562 | 16,614 |

## 5.1. ከ2013-2022 በጀት ዓመት የሚተገበሩ ፕሮጀክቶች

| ተ.ቁ | ፕሮጀክት አይነት | ጠቅላላ ፕሮጀክት ወጪ (ሚ. ብር) | በጀት ዓመት | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | 2019 | 2020 | 2021 | 2022 |
| | | | (ሚ. ብር) | (ሚ. ብር) | (ሚ. ብር) | (ሚ. ብር) | (ሚ. ብር) | (ሚ. ብር) | (ሚ. ብር) | (ሚ. ብር) | (ሚ. ብር) | (ሚ. ብር) |
| 1 | የቢሾፍቱ እንሳት ማእከል ቢሮ ግንባታ | 500 | - | | | | - | 250 | 250 | - | - | - |
| 2 | በቢሾፍቱ ማዕከል የላብራቶ ግንባታ | 7 | - | | | | - | - | 2.625 | 2.625 | 1.75 | - |
| 3 | ሞዴል ዘመናዊ አነስተኛ የንብ ውጤቶች ማቀነባበሪያ ግንባታና እቃ ማሟያ (30% USD) | 5.6 | - | | | | - | - | 2.1 | 1.75 | 1.75 | - |
| 4 | ሞዴል ዘመናዊ አነስተኛ አኳካልቸርና የዓሣ ሥጋ ማቀነባበሪያ ግንባታና እቃ ማሟያ (30% USD) | 7.7 | - | | | | - | - | 3.5 | 3.5 | 0.7 | - |
| 5 | ሞዴልና ዘመናዊ አነስተኛ የዶሮ ቁራና የዶሮ ምርት ውጤቶች ማቀነባበሪያ ግንባታና እቃ ማሟያ (30% USD) | 6.125 | - | | | | - | - | - | 2.625 | 1.75 | 1.75 |
| 6 | ሞዴልና ዘመናዊ የመኖ ሙከራና ማቀነባበሪያ ግንባታና እቃ ማሟያ (30% USD) | 6.125 | - | | | | - | - | 2.625 | 1.75 | 1.75 | - |
| 7 | የእንስሳት ዉጤቶችና ተዋፅዖ ምርት ፍተሻና ቤተ-ሙከራ ላብራቶሪ ግንባታና ዕቃና አደረጃጀት ማሙያ (40% USD) | 76.195 | - | | | | - | - | 43.75 | 26.25 | 6.195 | - |
| 8 | የኮርማ በረቶች ግንባታ | 50 | | | | | | 50 | | | | |
| 9 | የአባላዘር ላብራቶሪ ግንባታ | 100 | | | | | | 100 | | | | |

## 5.2. የሰው ሃይል ፍላጎት

| የትምህርት ደረጃ/የሙያ መስክ | ትንበያ | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | 2019 | 2020 | 2021 | 2022 |
| 4ኛ ክፍል ያጠናቀቀ/ች | 65 | 94 | 103 | 150 | 155 | 165 | 170 | 173 | 179 | 186 |
| 8ኛ ክፍል ያጠናቀቀ/ች | 95 | 100 | 125 | 168 | 205 | 211 | 217 | 225 | 231 | 242 |
| 10ኛ ክፍል ያጠናቀቀ/ች | 59 | 62 | 65 | 67 | 69 | 71 | 72 | 73 | 74 | 78 |
| መሰናዶ (12ኛ ክፍል) ያጠናቀቀ/ች | 72 | 85 | 91 | 100 | 112 | 115 | 120 | 125 | 130 | 135 |
| **በቴክኒክና ሙያ የተመረቀ/ች** | | | | | | | | | | |
| ደረጃ (level) 1 | 33 | 35 | 39 | 42 | 48 | 54 | 57 | 60 | 63 | 67 |
| ደረጃ (level) 2 | 35 | 38 | 43 | 48 | 544 | 60 | 65 | 70 | 75 | 80 |
| ደረጃ (level) 3 | 51 | 55 | 62 | 65 | 70 | 75 | 79 | 86 | 88 | 93 |
| ደረጃ (level) 4 | 40 | 47 | 55 | 64 | 74 | 95 | 106 | 119 | 127 | 130 |
| ደረጃ (level) 5 | 56 | 63 | 71 | 75 | 79 | 83 | 88 | 92 | 95 | 103 |
| **ኮሌጅ ዲፕሎማ** | | | | | | | | | | |

| የትምህርት ደረጃ/የሙያ መስክ | ትንበያ | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | **2013** | **2014** | **2015** | **2016** | **2017** | **2018** | **2019** | **2020** | **2021** | **2022** |
| በተፈጥሮ ሣይንስ/የሙያ መስክ | 63 | 70 | 73 | 77 | 80 | 85 | 90 | 94 | 104 | 114 |
| በማህበረሰብ ሣይንስ/የሙያ መስክ | 79 | 86 | 90 | 96 | 103 | 110 | 115 | 120 | 137 | 145 |
| **የመጀመሪያ ዲግሪ** | | | | | | | | | | |
| በተፈጥሮ ሣይንስ (BSc)/የሙያ መስክ | 250 | 320 | 380 | 450 | 489 | 550 | 600 | 613 | 653 | 718 |
| በማህበረሰብ ሣይንስ (BA)/የሙያ መስክ | 373 | 408 | 421 | 460 | 490 | 590 | 615 | 645 | 735 | 814 |
| **የማስተርስ ዲግሪ** | | | | | | | | | | |
| በተፈጥሮ ሣይንስ (MSc)/የሙያ መስክ | 140 | 181 | 204 | 217 | 227 | 238 | 253 | 270 | 302 | 315 |
| በማህበረሰብ ሣይንስ (MA)/የሙያ መስክ | 93 | 103 | 112 | 114 | 133 | 129 | 131 | 135 | 139 | 141 |
| **ፒኤችዲ (ዶክትሬት ዲግሪ)** | | | | | | | | | | |
| በተፈጥሮ ሣይንስ/የሙያ መስክ | 17 | 34 | 50 | 55 | 57 | 60 | 62 | 43 | 55 | 63 |
| በማህበረሰብ ሣይንስ/የሙያ መስክ | 2 | 3 | 5 | 7 | 9 | 12 | 13 | 14 | 16 | 29 |

**በኢ.ፌ.ዲ.ሪ እንስሳት ልማት ኢንስቲትዩት**
**F.D.R.E livestock Development institute**

ስ.ቁ 011 439 00 60
ፖ.ሳ.ቁ 22692
ቲውተር @livestockdevel
facebook livestock development institute
w.w.w ldi.gov.et
ዋና መ/ቤት ቃሊቲ ሸዋ ዳቦ አካባቢ

Beminet Printing Press PLC